www.ethiopianorthodox.org

# የምስጋና ሕይወት

የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ
ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ እንደጻፉት

ትርጉም፡- ዲ/ን ዘኤልያስ ወ/ሚካኤል

ሚያዝያ 2000

የተርጓሚው አድራሻ
0912-053260
✉ 23077/1000

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

## የዚህ መጽሐፍ ታሪክ

በ1965 ዓ.ም. እስክንድርያ በሚገኘው ቅዱስ ሚና ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተካሄደው የሰንበት ት/ቤት መምህራን ስብሰባ ላይ በምስጋና ሕይወት ላይ ያተኮረ ትምህርት ሰጠሁ:: ይህም ከሌሎች ትምህርቶች ጋር በመሆን በአነስተኛ መጽሐፍ መልኩ ለህትመት በቃ::

አርብ ግንቦት 16 ቀን 1980 ዓ.ም. ካይሮ በሚገኘው የቅዱስ ማርቆስ ካቴድራል ሌላ ትምህርት ሰጠሁ ርእሱም *«ስለ ሁሉ ነገር ስመስገን»* /ኤፌ 5፣20/ የሚል ሲሆን ይህ ትምህርት ግን አልታተመም ነበር::

ከዚህ በተጨማሪ በታህሳስ 31 ቀን 1980 ዓ.ም. የአዲስ ዓመት በዓልን ምክንያት በማድረግ በዋናነት *«የምስጋና ሕይወት»* ላይ በውስጡ ግን ራስን በማስገዛት እና በተስፋ ሕይወት ላይ ያተኮረ ለህትመት ግን ያልበቃ ትምህርት ቅዱስ ማርቆስ ካቴድራል ላይ ሰጥቻለሁ::

ወደ ሩሲያ ባደረግሁት ጉዞ ሌሎች ብዙ ጠቃሚ ትምህርቶችን ጨምሮ ከላይ የተጠቀሱትን ሦስት ትምህርቶች የምስጋና ሕይወት በሚል ርእስ በአንድ መጽሐፍ አዘጋጅቼ አሁን በእጃችሁ ያለውን መጽሐፍ እንዳቀርብ እግዚአብሔር ጊዜ ሰጠኝ::

በ1964 ቅዱስ ማርቆስ ካቴድራል ላይ የተሰጠውን የመጀመሪያ ትምህርት በምስጋና ፀሎት ላይ የተደረገ ጥናት በሚል ርዕስ አንድ መጽሐፍ በ1965 አሳትመናል:: ይህ መጽሐፍ እስክንድርያ በምትገኘው ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን አማካኝነት ለብዙ ጊዜያት ታትሟል:: እግዚአብሔር ቢፈቅድ ከዚህ መጽሐፍ መካከል የምስጋና ፀሎት የሚለውን ከሌሎች ፀሎቶች ጋር በማዋሐድ ለማሳተም ተስፋ አድርገናል::

እግዚአብሔር ይርዳን
አቡነ ሺኖዳ ሳልሳዊ
ሞስኮ፣ ሰኔ 1988 ዓ.ም.



## ምዕራፍ አንድ

### የምስጋና ሕይወት

የምስጋና ሕይወት የሚኖር ሰው የተደረገለትን ሥራ እና የተፈጸመለትን መልካም ነገር ሁሉ የማይረሳ ለዚህም ምስጋናውን በደስታ የሚገልጽ አዋቂ ሰው ነው:: ለእግዚአብሔር እና ለሰዎች የሚያቀርበው ምስጋና በልቡ ጽላት ላይ ተጽፎ የተቀመጠ በመሆኑ ምስጋና ከአንደበቱ ፈጽሞ ጠፍቶ አያውቅም::

ኢየሱስ ክርስቶስ ካነጻቸው ከአስሩ ለምጻሞች መካከል አንዱን ባርኮታል:: ከእነርሱም አንዱ እንደተፈወሰ ባየ ጊዜ «በታላቅ ድምጽ እግዚአብሔርን እያከበረ ተመለሰ፣ እየመሰገነውም በእግሩ ፊት በግንባሩ ወደቀ፤» ኢየሱስም መልሶ «አሥሩ አልነጹምን? ዘጠኙስ ወዴት አሉ? ከዚህ ከልዩ ወገን በቀር እግዚአብሔርን ሊያከብሩ የተመለሱ አልተገኙም» አለ:: /ሉቃ 17፣15-18/ ስለዚህ ለተደረገልህ ነገር ምስጋና ስታቀርብ እግዚአብሔርን እያከበርህ፣ ለአንተ የሰጠህን ፍቅሩን እና ትህትናውንም እየገለጽህ መሆንህን ተረዳ:: እግዚአብሔር በማንም በኩል አንድ መልካም ነገር

www.ethiopianorthodox.org



ካደረገልህ ከእግዚአብሔር በተጨማሪ ያንን መልካም ነገር እንድትቀበል ምክንያት ለሆነህ ሰውም ምስጋና ስጥ፡፡

ብዙ ሰዎች በየእለቱ መጀመሪያና መጨረሻ ላይ፣ በታላላቅ ክብረ በዓላት ላይ፣ እና በሕይወታቸው በሚያጋጥሟቸው ዋና ዋና ጊዜያት ላይ ብቻ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሰጣሉ፡፡ ነገር ግን «ሁልጊዜ ስለሁሉ አመስግኑ» /ኤፌ 5፣20/ የሚለው የሐዋርያው ቃል በቀዳሚነት የምንመራበት ቢሆንም የምስጋና ሕይወት የራሱ ባሕርያት አሉት፡፡

ሁልጊዜ አመስግኑ

ለእግዚአብሔር ምስጋና ስናቀርብ ጊዜና ወቅት ጠብቀን በተለየ ጊዜ ሳይሆን «ሁልጊዜ» መሆን አለበት፡፡ ምስጋናውም ደግሞ የማያቋርጥ እስከሆነ ድረስ መላ የሕይወት ዘመንን ያጠቃልላል፡፡ መላ ሕይወትን ከሚያጠቃልል የምስጋና ሕይወት ጋር ተመሳሳይ የሆነ ትምህርት በመጀመሪያዪቱ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች መልእክት ውስጥ «ሁልጊዜ ደስ ይበላችሁ፤ ሳታቋርጡ ጸልዩ፤ በሁሉ አመስግኑ፤» /1 ተሰ 5፣16-18/ ተብሎ ተገልጿል፡፡ ይህ ትምህርት የምስጋና ጸሎት ጸሎቶችን ሁሉ እንደሚመራ





ያስረዳል፡፡ የሠርክ እና የነግህ ጸሎቶችን ጨምሮ ሁሉም የቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶችና አገልግሎቶች የሚጀምሩት በምስጋና ጸሎት ነው፡፡ እግዚአብሔርን ሁልጊዜ በማለዳ በቀትር እና በማታ እናመሰግነዋለን፡፡ እንደ መዝሙረኛው ዳዊትም «ስለቅን ፍርድህ ለምስጋና በሌሊት እነሳለሁ» እንላለን፡፡ ከአጠቃላዩ የምስጋና ጸሎት በተጨማሪ በሰአት ከፋፍለን እናመሰግነዋለን፡፡

በመጀመሪያው ሰአት ጸሎት ላይ «ዘላለማዊው ንጉሥ ሆይ ... ሌሊቱን በሰላም አሳልፈህ ቀኑን ባርከህ ስለሰጠኸን እናመሰግንሃለን» እንለዋለን፡፡ ... ሌሊቱን በሰላም ጠብቆ በሕይወታችን አዲሱን ቀን ስለሰጠን እናመሰግነዋለን፡፡

በሦስተኛው ሰአት ጸሎት ላይ «በእያንዳንዳችን ላይ፣ በደቀ መዛሙርቶችህ ላይ፣ በተከበሩት ሐዋርያቶችህም ላይ ቅዱስ መንፈስህን እንደ እሳት ልሳኖች አፍስሰህ በዚህች በተቀደሰች ሰአት ለጸሎት ስላነሳሳኸን እናመሰግንሃለን» እንላለን፡፡

በስድስተኛው ሰአት ላይ «የአምላካችን እና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ገናናው ንጉሣችን ሆይ እናመሰግንሃለን፣ የአንድያ ልጅህን የመከራ፣ የጸሎት

www.ethiopianorthodox.org



እና የእረፍት ሰአት የምናስብበትን ስለአዘጋጀህ እናከብርሃለን» እንለዋለን።

ፀሐይ ስትጠልቅም «ተወዳጁ ንጉሣችን ሆይ፣ ይህ ቀን በሰላም እንዲያልፍ ስለፈቀድህልንና በምስጋና ወደዚህ ምሽት ስላደረስኸን ፀሐይም እስክትጠልቅ ድረስ ብርሃን እንድናይ ስላበቃኸን እናመሰግናለን» እንላለን።

እግዚአብሔርን በሰላም ስላለፈችው ስለእያንዳንዷ ሰአት እናመሰግነዋለን። ይህም በእያንዳንዱ ጸሎት መጀመሪያም ላይ ሆነ በተወሰኑ ጊዜያት ላይ ሳይቋረጥ የሚሰጥ ምስጋና ነው።

ስለሁሉ አመስግኑ

ቤተ ክርስቲያናችን የቀብር ስርዓትን እንኳን ሳይቀር የምትጀምረው በምስጋና ጸሎት ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «በቃል ቢሆን ወይም በሥራ የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉት።» /ቈላ 3፥17/ ብሏልና በማንኛውም ጊዜ በምንም አይነት ሁኔታ ውስጥ ሆነን ስለሁሉም ነገር እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን። ስለዚህ እግዚአብሔርን ሁልጊዜ ብቻ ሳይሆን ስለሁሉም ነገር ጭምርም ማመስገን ያስፈልጋል። ምክንያቱም ሐዋርያው





«እግዚአብሔርም ለሚወዱት እንደአሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን።» /ሮሜ 8፥28/ እንዳለ እግዚአብሔር ያለማቋረጥ በጎ ነገር ያደርግልናል።

በዚህ ምክንያት እግዚአብሔርን «ጥቅማችን ነው» እያልን እንጠራዋለን። እርሱ ከበጎ ነገር ውጪ አያደርግም በዚህ የሚያምን ሰውም ከእግዚአብሔር የሚመጣውን ማንኛውንም ነገር ሁሉ በደስታ ከመቀበሉም በላይ በእምነት «...ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ አውቃለሁ» ይላል እግዚአብሔርንም ያመሰግናል። ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች፦ «ከእግዚአብሔር የሚመጣ ሁሉ በጎ እንደሆነ ያለመጠራጠር እናምናለን፣ ነገር ግን ከሰዎች የሚመጣውን እና ሙሉ ለሙሉ በጎ ሊሆን የማይችለውን እንዴት እናምናለን?» ብለው ሊጠይቁና ሊናገሩ ይችላሉ። ለእነዚህ ሰዎች «ሰዎች ለኛ ያላቸው አመለካከት በጎ ከሆነ በጎ ሆኖ ወደእኛ ይደርሳል በጎ ካልሆነ ግን እግዚአብሔር ይለውጠዋል በመጨረሻም በጎ ሆኖ ወደእኛ ይደርሳል» እንበላቸው።

የጻድቁ የዮሴፍ ወንድሞች እርሱን እንደ ባሪያ በሸጡት ጊዜ ሥራቸው በራሱ ክፋት፣ ፍቅር ማጣት ጭካኔ እና ምቀኝነት ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ያንን የክፋት

www.ethiopianorthodox.org



ሥራቸውን ወደበጎ ስለለወጠው ዮሴፍ በፈርዖን ቤት ላይ ተሾሞ ሕዝቡም ሁሉ ለቃሉ ታዛዥ ሆነው ነበር። በዚህ ጊዜ በፈርዖን መንግሥት ሁለተኛ ባለሥልጣን የነበረ ሲሆን በግብጽ ቆይታውም የብዙ ሰዎችን ሕይወት አትርፏል። ከዚህ በመነሳትም ዮሴፍ ለወንድሞቹ «እናንተ ክፉ ነገርን አሰባችሁብኝ እግዚአብሔር ግን ብዙ ሕዝብ እንዲድን ለማድረግ ለመልካም አሰበው» /ዘፍ 45/ አላቸው።

የእግዚአብሔር ልጆች ሁልጊዜ ደስተኞች በመሆናቸው ስለሁሉ ነገር እርሱን ያመሰግኑታል። ሲያመሰግኑትም «አመስግኑ» የሚለውን ትእዛዝ እንደግዴታ በመመልከት አይደለም። ምክንያቱም በግዴታ የሚደረግ ምስጋና እውነተኛ ምስጋና አይደለም። ነገር ግን እግዚአብሔርን በእውነተኛ ምስጋና የሚያመሰግኑ ሁሉ ከልባቸው በሙሉ ፈቃድ ያመሰግኑታል። እግዚአብሔር መጥፎ የሆነ ነገር ሁሉ በእነርሱ ላይ እንዲደርስባቸው እንደማይፈቅድ፣ ከሚገጥሙአቸው ችግሮች ሁሉ ክብር በመሆን እንደሚጠብቃቸው እና በሥራቸው ሁሉ እገዛን እንደሚያደርግላቸው ፍፁም የሆነ እምነት አላቸው።ስለዚህ ወደፊት ከምስጋና ጋር ግንኙነት ስላላቸው





ምግባራት በምንነጋገርበት ጊዜ እንደምናየው የምስጋና ሕይወት በእምነት ሕይወት የታገዘ ነው።

ሰው እግዚአብሔርን በቃላት ማመስገን ይችላል። ነቢዩ ዳዊት «የመድኃኒትን ጽዋ እቀበላለሁ፣ የእግዚአብሔርንም ስም እጠራለሁ። በሕዝቡ ሁሉ ፊት ስእለቴን ለእግዚአብሔር እፈጽማለሁ።» /መዝ 116፣13/14/ እንዳለውም የምስጋና መሥዋእት ወይም የስእለት መሥዋእት ማቅረብ ይችላል።

## የምስጋና ደረጃዎች

የእግዚአብሔር ልጆች በሕይወታቸው ውስጥ የሚፈጽሙት ምስጋና በተለያየ ደረጃ የሚፈፀም ነው።

ከነዚህ ውስጥ ትንሹ ማንም ሰው መልካምነታቸውንና ጥቅማቸውን ለማይጠራጠርባቸው እና ማራኪ ለሆኑ መልካም ነገሮች የሚሰጥ ምስጋና ነው። አንዳንድ ሰዎች ከነዚህ ውጪ ለሆኑት ነገሮች ምናልባት ላያመሰግኑ ይችላሉ። እነዚህ ሰዎች የተለያዩ የደስታ ዓይነቶችን ሊያሳልፉ ሌሎች መልካም ነገሮችንም ተፈጥሮአዊ እና የተለመዱ ምስጋናም የማያስፈልጋቸው አድርገው

www.ethiopianorthodox.org



ሊመለከቱአቸው ይችላሉ:: ነገር ግን ትንሽ በሆነው ነገር ምስጋና ሊሰጠው የሚገባው ከፍተኛ የምስጋና ደረጃ አለ::

እንደ ካንሰር ካለ አደገኛ ሕመም መዳንን ምክንያት በማድረግ የሚሰጥ ምስጋና በምስጋና ሕይወት ውስጥ የተለመደ የምስጋና ደረጃ ነው:: ነገር ግን አንድ ሰው ከጉንፋን ወይም ከቀላል ብርድ በመዳኑ ምክንያት ካመሰገነ በሕይወቱ ውስጥ ለብዙ ነገር ወይም ለትንንሽ ነገሮች የሚያመሰግን መሆኑን ያመለክታል::

በትንንሽ ነገሮች የምናመሰግን ከሆነ እግዚአብሔር በብዙ ነገር ላይ ገዢዎች አድርጎ ይሾመናል:: ቅዱሳን አባቶች «ጸጋ ያለምስጋና አያድግም» ሲሉ እንደተናገሩት ምስጋና የማያቋርጥ በረከት ያለው እና በረከቱም ሁልጊዜ የሚያድግ መሆኑ የምስጋና ጥቅሞች ብዙዎች መሆናቸውን ያሳያል::

ስውር ለሆነውና ለማይታየው በረከትም የሚሰጥ ምስጋና ደግሞ አለ:: እግዚአብሔር እኛን ከለመጠበቁ እና ለእኛ ካለመጨነቁ የተነሣ ሳይሆን ለጥቅማችን ሲባል ሊደርሱብን ለሚችሉት መከራዎችና ችግሮች ምስጋና ይገባል:: ማየት ባንችልም እንኳን እግዚአብሔር





እንደሚያደርገው ሙሉ ለሙሉ ለምናምንበት ሥራ ምስጋና ይገባል::

ያለምንም ጥርጥር ሰይጣን እኛን ለመጉዳት እና ለመጣል ከፍተኛ ሥራውን እየሠራ ባለበት በአሁኑ ሰአት ደህና ከሆንን እኛ የማናውቀውን የሰይጣን ተንኮል እግዚአብሔር ስላቆመልን ነውና በእግዚአብሔር ባለፍናቸው መከራዎች ውስጥ እግዚአብሔርን እናመስግነው:: ነገር ግን ወደ እኛ ከመድረሳቸው በፊት በመንገድ ያስቀራቸው ብዙ ችግሮች እንዳሉ ደግሞ መዘንጋት የለብንም:: እነዚህን ችግሮች እኛ ባናውቃቸውም ከነርሱ ስለጠበቀን ግን እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን::

እግዚአብሔርን ስላዳነን የምናመሰግነው ምስጋና ከደረሰብን ችግር ስለሚያድነን ሲሆን ስለጠበቀን የምንሰጠው ምስጋና ግን ማየት ከማንችለው ችግር ስለሚጠብቀን ነው::

በእግዚአብሔር ጊዜ ዘግይተን ለምናውቃቸው ወይም ፈጽመን ልናውቃቸው ለማንችላቸው የርሱ ስውር እውቀት ለሆኑት ነገሮች እናመስግነው::

በዚህ ሁሉ ጊዜ ምስጋና ከፍቅር ጋር ሊዋሃድ ይገባዋል:: ሌላው የምስጋና ደረጃ አንድ ሰው መላ ሕይወቱ

www.ethiopianorthodox.org



በምንም አይነት ሁኔታ ውስጥ ቢኖር እንኳን ሁልጊዜ ስለሁሉም ነገር ምስጋና የሚሰጥበት ደረጃ ነው:: ቋሚ የሆነ ምስጋና የተለየ ምክንያት አይፈልግም:: ነገር ግን በእግዚአብሔር ጥበቃ ስር የምንኖር ልጆቹ መሆናችን እና ይህ የእግዚአብሔር ልጅነት ራስን ለእግዚአብሔር ከማስገዛት ሕይወት ጋር መስማማቱ በቂ ነው:: ስለዚህ ምስጋናችን እኛ በምናገኛቸው የተለያዩ ገጠመኞች ላይ የተመሠረተ መሆን የለበትም::

ስለደረሰባችሁ መከራዎች አመስግኑ

ከፍተኛው የምስጋና ደረጃ በመከራ ሰአት ማመስገን ነው እግዚአብሔርን ከደረሱብን መከራዎች ሰላዳነን እናመሰግነዋለን:: ይህም ምስጋና ትንሹ የምስጋና ደረጃ ነው:: ከዚህ የሚበልጠው ምስጋና ግን ተሸከመናቸው ስለምንኖርባቸው ስለደረሱብን መከራዎች እግዚአብሔርን ማመስገን ነው:: ይህም ለመልካም እንዲደረግብን በእምነት እናምናለን:: መከራዎችን መታገስ እና መሸከም አንድ ትልቅ ምግባር ነው:: በመከራ ውስጥ ማለፍና መከራን መቀበልም እንዲሁ ከታላቅ ምግባር የሚመደብ ሲሆን የበለጠ ጠቃሚው





ነገር ግን በመከራ ጊዜ እንደግዴታ ሳይቆጥሩ በደስታ ማመስገን ነው::

እመኑኝ ስለተቀበልናቸው ስጦታዎች ብቻ የምናመሰግን ከሆነ ፍቅራችንን የምንገልፀው ስጦታዎቹን ለሰጠን ለእግዚአብሔር ሳይሆን ለተሰጡን ስጦታዎች ብቻ ይሆናል:: ነገር ግን በመከራ ውስጥ እግዚአብሔርን የምናመሰግን ከሆነ ስጦታዎቹን ሳይሆን ራሱን እግዚአብሔርን መውደዳችንን እናረጋግጣለን:: ማለትም እርሱን የምንወደው እና ዓላማችን ያደረግነው ሀብት፣ ክብር፣ የተመቻቸ ሕይወት ስለሰጠን ብቻ ሳይሆን የጸጥታ እና የሰላም ባለቤቶች ስላደረገን፣ ወደ በጎ የሚለውጣቸውን የተለያዩ መከራዎችንም ስለሰጠን እንወደዋለን በእያንዳንዱ ሁኔታ ላይም እናመሰግነዋለን ከዚህ በተጨማሪ በሕይወታችን ምንም አይነት ችግር ቢከሰትብን እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን:: በእግዚአብሔር ጥበቃ ላይ ያለንን እምነት እና ለእርሱ ማቅረብ የሚገባንን ምስጋና የምናውቅበትን ትምህርት ለሚሸረሽሩብን መሰናክሎችም መንገድ አንከፍትላቸውም::

www.ethiopianorthodox.org



እንደነዚህ አይነት አጋጣሚዎች በጌታ የምናገኘውን ሰላማችንን እና ደስታችንን እንዲነጥቁብን አንፈቅድላቸውም ይህንን ስናደርግ ውጪያዊ ሁኔታችን ምንም ይሁን ምን ሁልጊዜ በጌታ ደስ ይለናል ከእግዚአብሔርና ከሰዎች ጋርም በሰላም እንኖራለን::

ይህ ምስጋናችን እና ደስታችን በሌሎች ላይ ተጽእኖ ይፈጥራል:: ስለዚህ ሰዎች ስለሚደርሱብን መከራዎች የምናቀርበውን ምስጋናችንን ጸጥታችንን እና ደስታችንን ሲመለከቱ ጽናትን ያገኛሉ በርግጠኝነት የልባችንን ሰላም ሲመለከቱም በሚቀርቡልን መንፈሳዊ መመሪያዎች ይማረካሉ:: ነገር ግን ይህን ሁሉ የምናደርገው በሕይወታችንና በጠባያችን ለነርሱ ምሳሌዎች ሆነን ለመገኘት ነው:: የመንፈስ ፍሬዎች ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም ናቸው ተብሎ ተገልጿል:: እነዚህን ፍሬያት ያገኘ ለእግዚአብሔር ምስጋና ያቀርባል::

በተጨማሪም መከራዎች መንፈሳዊነትን ስለሚያጠነክሩ ምስጋና ያስፈልጋቸዋል:: ምስጋና አንድን ሰው በጸሎቱ፣ ከእግዚአብሔር ጋር በሚኖረው ግንኙነት፣ በጾሙ እና በእምነቱ የጠለቀ እንዲሆን ያደርገዋል:: የእግዚአብሔር





ልጆችን ልቦች ወደ እግዚአብሔር ከፍ አድርጎ ያገናኛል:: በመከራ የታጠረ የሕይወት አንድን ሰው በመቶዎች ከሚቆጠሩ ስብከቶች እና በርካታ መንፈሳዊ መጻሕፍትን ከማንበብ የበለጠ ወደ ንስሐ ሕይወት ይመራዋል::

የእግዚአብሔርን እጆች በመከራ ውስጥ ሲሰሩ እናያቸዋለን:: መከራ አምላካችንንና ሥራዎቹን፣ ወደ ሕይወታችን የሚያደርገውን መምጣቱን እና ጥበቃውን ያሳዩናል:: መከራ የእግዚአብሔርን ኃይል እና ድንቅ ሥራዎች እንድናይ ያደርገናል:: ያለመከራ ልናገኛቸው የማንችላቸውን መንፈሳዊ ልምዶች ይሰጠናል:: ዳግመኛም መከራ ስንዴውን ከእንክርዳድ ለይቶ ቤተ ክርስቲያንን ያጠራታል::

ለነዚህና ለሌሎችም ምክንያቶች ሁሉ ስለሚደርሱብን መከራዎች እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን:: እነዚህን መከራዎችም እንደ በረከት እንቆጥራቸዋለን:: በእርግጥ ስለሚደርስበት መከራ የሚያመሰግን ስለሌሎች ስለሁሉም ነገሮች ያመሰግናል:: ስለዚህ እንደዚህ ዓይነት ሰው የማይናወጥ የምስጋና ሕይወት ይኖራል እንጂ ፈጽሞ አያዝንም::

www.ethiopianorthodox.org



## ምስጋና የሚገባቸው መከራዎች

በምሳሌ አጉልቶ ለማስቀመጥ፣ አባቶቻችን ሐዋርያት ታስረው እና ተገርፈው በተፈቱ ጊዜ «ስለስሙ ይናቁ ዘንድ የተገባቸው ሆነው ስለተቆጠሩ ከሸንጎው ፊት ደስ እያላቸው ወጡ» /ሐዋ 5፣41/ ይላል:: ስለዚህ አባቶቻችን ሐዋርያት እነዚህን ሁሉ ስቃዮች እና ስድቦች ለነርሱ የማይገቡ በረከቶች አድርገው ቆጥረዋቸዋል:: ምክንያቱም እነዚህን መከራዎች መቀበል የክርስቶስን መከራዎች ከመካፈል የሚቆጠር ነውና:: መጽሐፍ ቅዱስ «ይህ ስለ ክርስቶስ ተሰጥቶአችኋልና፤ ስለእርሱ መከራ ደግሞ ልትቀበሉ እንጂ በእርሱ ልታምኑ ብቻ አይደለም፤» /ፊል 1፣29/ ይላል::

ስለዚህ፣ መከራዎች ስጦታዎች ናቸው:: ስጦታዎች እስከሆኑ ድረስ ደግሞ፣ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፤ «እርሱንና የተንሣኤውን ኃይል እንዳውቅ፣ በመከራውም እንድካፈል፣ ... በሞቱ እንድመስለው» /ፊል 3፣10/ ብሎ እንደጻፈ እኛስ ለምን አንደሰትባቸውም ለምንስ ምስጋና አናቀርብባቸውም? አባቶቻችን ሐዋርያት የተደሰቱባቸው እና የተካፈሉአቸው መከራዎች ናቸውና::





አንድ መንፈሳዊ ሰው አምላኩ «መስቀሌን ተሸከም» ብሎ ከሰጠው የክርስቶስን ስቃይ መካፈል ስለሆነ በደስታና በምስጋና ሊቀበለው ይገባል::ልክ በስጦታዎች ምስጋና እንደሚያቀርብ ሁሉ ለሚቀበላቸው መከራዎችም እንዲሁ ምስጋና ሊሰጥ ይገባዋል ምክንያቱም መከራም ስጦታ ነው::

ብዙዎቹ መከራ ሲደርስባቸው በስቃዮቹ እና በሕመሞቹ ላይ ያተኩራሉ መንፈሳውያን ግን የሚያተኩሩት አምላካችን እግዚአብሔር እነዚህን መከራዎች እንዲደርሱብን የፈቀደው ለምንድን ነው? በሚለው ላይ ነው:: በምንቀበላቸው በሁሉም መከራዎች ውስጥ መልካም የሆነ ነገር አለ:: በውስጣቸው ያለውን መልካም ነገር ወዲያውኑ ማየት ባንችል እንኳን መልካም የሆነ ነገር በውስጣቸው የለም ማለት አይደለም:: ምክንያቱም በአይናችን ማየት ያልቻልነውን ነገር በእምነት ማየት እንችላለን::

ከነቢዩ ዮናስ ኀዘኖች እና መሰናክሎች ብዙ ትምህርት መማር እንችላለን:: ዮናስ በዓሣ አንበሪ ተውጦ በነበረ ጊዜ እግዚአብሔርን አመስግኗል? አዎ! አመስግኗል:: ምክንያቱም ከሸሸት የጠበቀው እና ተልእኮውን እንዲፈጽም

www.ethiopianorthodox.org



ለነነዌም ድኅነት እንዲያለቅስ ያደረገው ብቸኛው መንገድ ይህ ምስጋናው ነው፡፡ ዮናስ ለራሱ ጥላ የሰጠችው ቅል በደረቀች ጊዜ አዝኖ እንደነበር እናስታውሳለን፡፡ ነገር ግን መንፈሳዊ እይታውን አርቆ ካስተዋለ የዛፏ መድረቅ ከእግዚአብሔር ጋር ለሚፈጽመው እርቅ መነሻ እና እግዚአብሔርን ስለደረሰበት መከራም ሊያመሰግን ከሚገደድበት ነገር አንዱ መሆኑን ያስተውላል፡፡

የቅዱስ እንጦንስ አባት መሞት ምስጋና ለማቅረብ ምክንያት ይሆን ነበር? በአሁኑ ሰአት ለአባቱ ሞት ምክንያት ምስጋና የሚያቀርብ ልጅ የት አለ? ቅዱስ እንጦንስ በአባቱ መሞት ምክንያት ምስጋና ማቅረቡ ተገቢ ነበረ ማመስገን የሚባን እኛ ነበርን፡፡ ምክንያቱም የዚህ ሰው አባት መሞት ይህን ጻድቅና ቅዱስ ወጣት ሰው በምድራዊ ሕይወት አስቸጋሪነት ላይ በትኩረት እንዲያስብበት አድርጎታል፡፡ ወደ ምንኩስና ሕይወት እንዲገባም በቅድሚያ ያነሳሳው ይህ ነበር፡፡ በአባቱ ሞት ጊዜ ወደ አባቱ አካል በመመልከትና «ክብርህ፣ ኃይልህና ባለጸግነትህ ወዴት አለ? ያለፈቃድህም ከዚህ ዓለም በሞት





ተነጠቅህ ስለዚህ ሞት እኔን ያለፈቃዴ ከመውሰዱ በፊት እኔው በራሴ ፈቃድ እሄዳለሁ» በማለት ይህንን መልአካዊ ሥርዓት የሆነ የምንኩስና ሕይወት መሠረተልን ዓለምንም ትቶ የመነኮሳት ሁሉ አባት ለመሆን በቃ፡፡

ፍቁረ እግዚእ ዮሐንስ ወደ ፍጥሞ ደሴት በመሰደዱ ምክንያት እግዚአብሔርን ማመስገን አለብን ብላችሁ ታስባላችሁ? ያለምንም ጥርጥር መልሱ አዎ ነው፡፡ ምክንያቱም በስደቱ የተቀበለው መከራ «በጌታ ቀን በመንፈስ ነበርሁ» /ራዕ 1፣10/ እስከሚል ድረስ መንፈሱን ለጌታ አስነስቶ በስደቱ ወቅት ሰማያት ተከፍተው የእግዚአብሔርም ዙፋን በሰማያዊ ኃይላት ተከብቦ ተመለከተ፡፡ በመጨረሻም የሆነውን ሁሉ አይቶ የራእይ መጽሐፍን ጻፈ፡፡

የዮሐንስ የስደት ወቅት የሕይወቱ ምርጥ ጊዜ እና ምስጋና የሚገባው ዋና ጉዳይም እንደነበር ጥርጥር የለውም፡፡ ተስፋችንና ራእያችን በችግሮቻችን ብዛት ተወስኖ የሚቀር ሳይሆን ከነርሱ የሚመጣውን ውጤት ለመቀበል አርቆ የሚመለከት እና እግዚአብሔር ከነርሱ ያዘጋጀውን ታላቅ በጎ ነገር የሚጠብቅ ነው፡፡ ችግርን በራሱ ማመስገን ባንችል

www.ethiopianorthodox.org



እንኳን ችግሩ ወደ መልካም እንደሚቀየር በማመን እናመስግን::

የዓለም ሰዎች በተለያዩ ኀዘኖችና መሰናክሎች ውስጥ በሚወድቁ ጊዜ የምስጋና ስሜቶቻቸውን ሊያጡ ይችላሉ:: ከመካከላቸውም አንዱን ለእግዚአብሔር ምስጋና እንዲያቀርብ ብትጠይቀው በቁጣና በንዴት «ለምኑ ነው የማመሰግነው? በውስጤ ያለው ብሶት አይታይህምን?» ብሎ ሊመልስልህ ይችላል:: ነገር ግን ቅዱሳን የሆኑ የእግዚአብሔር ልጆች በእንደዚህ አይነት ነገሮች አይጨነቁም:: ምክንያቱም ብቸኛ ጭንቀታቸው ከእግዚአብሔር መለየታቸው ብቻ ነው:: ስለዚህ ከእርሱ ጋር እስከኖሩ ድረስ ግን ቋሚ ለሆነ የምስጋና ሕይወት ይህ በቂያቸው ነው:: በእያንዳንዱ ሁኔታ፣ በድህነታቸው፣ በባለጠግነታቸው፣ በሕመማቸው እና በጤንነታቸው፣ በሕይወታቸው እና በሞታቸው ጊዜ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል::

እነዚህ ሰዎች ዋና ዓላማቸው የሆነውን ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነት ባለማጣታቸው ሁልጊዜ ደስተኞችና ሐሴትን የተሞሉ ሆነው ታያቸዋለህ::





በዚህ ሁሉ ምክንያትም ሁልጊዜ ያመሰግናሉ:: እያንዳንዳቸውም «ሁሉን ነገር አጥቼ እግዚአብሔር ብቻ ቢቀረኝ ይህ በቂዬ ነው፣ እግዚአብሔር ለኔ ሁሉ ነገሬ፣ ሁሉ በሁሉ ስለሆነ የሚያስፈራኝ የለም፣ ለዚህም አመሰግነዋለሁ» ይላሉ:: ለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ስለዚህ ነው ክርስቶስ በድካም በመንገላታትም በችግርም በስደትም በጭንቀትም ደስ ይለኛል» /2 ቆሮ 12፤10/ ያለው:: ጭንቀት ወደ እግዚአብሔር የበለጠ ስለሚያቀርበው ደስ ይለዋል፣ በዚህ ጊዜም ፈጥኖ «ስደክም ያን ጊዜ ኃይለኛ ነኝና» ይላል:: ከዚህ በተጨማሪ ከተቋቋማቸው መከራዎች አክሊሎችን ይቀዳጃል::

አንድ መንፈሳዊ ሰው ስቃይ የተሞላበት መከራ ቢደርስበት «ከዚህ መከራ ባሻገር በጎ ነገር ባይኖር ኖሮ እግዚአብሔር ይህ እንዲደርስብኝ አይፈቅድም ነበር፤ ስለዚህ በደስታ እቀበለዋለሁ» ይላል::

## ወሰን የሌለው ምስጋና

አንድ ሰው እውነተኛ የምስጋና ሕይወት ከኖረ፤ በሚተነፍሰው በእያንዳንዱ ትንፋሽ፣ በሚራመደው በእያንዳንዱ እርምጃ፣ በሚሠራው በእያንዳንዱ ሥራ እና

www.ethiopianorthodox.org



ወደ እርሱ በሚመጣው በእያንዳንዱ ነገር እግዚአብሔርን ያመሰግናል:: ምስጋና የማያስፈልገውን ማንኛውንም ነገር አይመለከትም ነገር ግን በእርሱ ስለሚደርስበት ስለሁሉም ነገር «ነገር ሁሉ ለበጎ ነው» ይላል::





## ምዕራፍ ሁለት

## የምስጋና መስኮች

ለእግዚአብሔር ምስጋና የምንሰጥባቸው ወይም ለምስጋና የሚበቁ ብዙ ምክንያቶች ያሉ ሲሆን እኛ ግን የምንፈጽማቸው በአነስተኛ ሁኔታ ነው:: አንዳንዶቹ ምክንያቶች ፍፁም የተለመዱ ነገሮች ሲመስሉ ሌሎቹ ደግሞ ደስተኛ ያደርጉናል ያስደንቁናልም ነገር ግን ምስጋና አናቀርብባቸውም:: በሦስተኛ ደረጃ በአጋጣሚ ምስጋና የምናቀርብባቸው የእግዚአብሔር ሥራና ትሕትና በግልጽ የሚታይባቸው ጉዳዮች አሉ::

በዚህ ምእራፍ ውስጥም የተወሰኑትን የምስጋና ምክንያቶች ለማቅረብ እንሞክራለን::

1. እግዚአብሔርን ስለፈጠረህ እና ሕልውና ስለሰጠህ አመስግነው፣

እውነቱን ስንነጋገር፣ ስለፈጠረውና ሕይወት ስለሰጠው እግዚአብሔርን የሚያመሰግን ሰው አለ? እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ ሕይወት አለመስጠት እና በአለም የሕዝብ ቁጥር ላይም አንድ ሰው እንኳን አለመጨመር ይችል ነበር:: ወላጅ እናትህ መካን ስላልሆነች እና የመውለድ በረከት ስለተሰጣት



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



እግዚአብሔርን አመስግን:: ልደትህ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ታላቅ በረከት ነው:: ለዚህም በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ «እነሆ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታዎች ናቸው» /መዝ 127፣3/ ተብሏል:: አባትህ ይህን ስጦታ መቃወም ወይም አንተን ሳይጨምር ወንድሞችህንና እህቶችህን ብቻ መውለድ ይችል ነበር:: ነገርግን ከታላቅ ርህራሄው የተነሳ ካለመኖር ወደመኖር አመጣህ::

2. በዙሪያህ ስላለው ፍጥረት እግዚአብሔርን አመስግነው፤

እኛን ሰዎችን በስድስተኛው ቀን ስለፈጠረን ሁላችንም እግዚአብሔርን ማመስገን ይገባናል:: እግዚአብሔር ሰውን ከመፍጠሩ በፊት ለሰው ምቾት በማሰብ አስቀድሞ ሁሉንም አዘጋጀለት:: ሰማይን ፈጥሮ በዚህ ድንቅ ዓለም ውስጥ የተፈጥሮ ዑደቶችን የሚያገናኙ የጠፈር ህጎችን አስቀመጠ:: ከከባቢ አየር፣ ከአየር ንብረት እና ከዝናብ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ነገሮች ስርአት አስያዘ:: በመቀጠልም ዕጽዋትንና እንስሳትን እንዲሁም በየብስ በሰማይ እና በባሕር የሚኖሩ ሌሎች ሕይወት ያላቸው ፍጥረታትን ፈጠረ:: ሰውንም ከመፍጠሩ በፊት ለሰው ምግቡን አዘጋጀለት:: የተፈጥሮ





አቀማመጥን፣ የአትክልት ሥፍራዎችን እና የአበቦችን ውበት እንዲሁም የአዕዋፋትን ዝማሬ ለሰው መደሰቻ አድርጎ ፈጠ ራቸው::

እነዚህን ሁሉ ምቹ ሁኔታዎች ካዘጋጀ በኋላ ሰውን ፈጠረው:: ለሰው ምቾች በቂ እና ዘርፈ ብዙ ለሆነው ለዚህ የተፈጥሮ ውበት እግዚአብሔርን የሚያመሰግን ማን ነው?

3. እግዚአብሔርን ስለሰጠህ ተፈጥሮአዊ ተሰጥኦዎችህ አመስግነው፣

ብዙ ሰዎች የታመመ መፈወስን፣ ሙት ማስነሳትን፣ መንፈሳዊ ራእይ እና ሕልም ማየትን የመሳሰሉ ከተፈጥሮ በላይ ለሆኑ ተሰጥኦዎች ካልሆነ በስተቀር አያመሰግኑም::

የፈውስ ስጦታዎችን ከመቀበል እና ተአምራትን ከማድረግ /1ቆሮ 12፣8-10/ አስቀድሞ በመጀመሪያ ደረጃ ሊቀመጡ ለሚገባቸው የጥበብና የእውቀት ተሰጥኦዎች እግዚአብሔርን የሚያመሰግን ማን ነው?

ለምሳሌ:- ጥበብ ወይም እውቀት ወይም ማስተዋል ስለሰጠህ እግዚአብሔርን አመስግነኸው ታውቃለህ ? ስእል የመሳል ፣ ግጥም ወይም ዜማ የመድረስ ተሰጥኦ ስለሰጠህ፣

www.ethiopianorthodox.org



ለጆሮ የሚጣፍጥ ድምጽ፣ ቆንጆ መልክ፣ ሰዎችን የማሳመን ችሎታ እና የመታገስ የመጽናትም ኃይል ስለሰጠህ እግዚአብሔርን አመስግነኸው ታውቃለህ? እነዚህ ሁሉ ስጦታዎች እግዚአብሔርን ልናመሰግንባቸው የሚገቡን ከእግዚአብሔር የተሰጡን ተሰጥኦዎች ናቸው::

4. ስላለህበት /ስለምትኖርበት/ እምነት እግዚአብሔርን አመስግነኸው ታውቃለህ ?

ወደ ክርስትና እምነት ለመቀላቀል ምንም ድካም ሳትደክም ክርስቲያን ሆነህ ስለተወለድህ እግዚአብሔርን አመስግነኸዋል ? ብዙ ሰዎች የክርስትና እምነትን ፈልገው ብዙ ቢደክሙም በርካታ የመሠረተ እምነት፣ የቤተሰብ፣ የአካባቢ እና ሌሎች ችግሮች ስላጋጠሙአቸው መድረስ እና ማግኘት አልቻሉም:: አንተ ግን ይህን እምነት በእምነት እና በአማኞች ውስጥ በመወለድህ በነፃነት እና በቀላሉ አግኝተኸዋል::

በጸሎት ላይ የነበረ ምዕመንን ተመልክቶ የተደነቀ የአንድ እምነት የለሽ ፈላስፋ ታሪክ ትልቅ ትምህርት ያስተምረናል:: ይህ ፈላስፋ ተራው ምዕመን መሬት ላይ ተንበርክኮ ማየት የማይችለውን አምላክ በሙሉ ልቡና ስሜት





በእምነት እንዴት እንደሚያነጋግር ከተመለከተ በኋላ «ፍልስፍናዬን እና ትምህርቴን ሁሉ ለማቆምና በምትኩም ይህ ተራ ሰው የተመሰጠበትን እምነት ለመከተል ተዘጋጅቻለሁ፤» አለ::

አንተ እየተከተልከው ያለኸው እምነት አማኞች በሌሉባቸው ሃገሮች እና አማኞች ባሉባቸው ሃገሮች ያሉ ከሃዲዎች ፈጽመው ሊያገኙት ያልቻሉት ጸጋ ነው:: ለእምነትህ ብቻ ሳይሆን እምነትህ ፍፁም ስለሆነም አመስግን:: ምክንያቱም የአንተ እምነት ብዙዎቹ ሰዎች በሚያደርጓቸው አንዳንድ ግንኙነቶች፣ በመጽሐፎች ወይም በአንዳንድ መጣጥፎች አማካይነት ከሌላ እምነት ጋር ሲጋጩ ከእምነታቸው እንደሚያፈነግጡበት ያለ እምነት አይደለም:: የእነርሱ እምነት ግን አስቀድሞ በተመሠረተው የሚጸና ሳይሆን በራሱ የእምነት መሠረቶች አማካይነት የሚለዋወጥ ነው:: ከእንደዚህ አይነት ጥርጣሬዎች የራቀ ፍፁም እምነት ውስጥ እየኖርህ በመሆንህ እግዚአብሔርን አመስግን::

www.ethiopianorthodox.org



5. እግዚአብሔርን እስከዚህች ሰዓት ድረስ እንድትኖር ስላደረገህ አመስግን፤

ይህ ምስጋና እግዚአብሔር «እዚህች ሰዓት ላይ ስላደረሰን» በምናመሰግንበት የምስጋና ጸሎት ውስጥ ተፈጽሞአል፡፡ ወንድሜ ሆይ፣ ሕይወትህን እርሱ ሊጠብቃት ወይም በማንኛውም ጊዜ ሊፈጽማት ይችላል፡፡ ለምትኖርባት ለዛሬዋ እለት ያደረሰህን እና መንፈሳዊ ደረጃህን የምታሳድግበትን እንዲሁም መልካም ነገር የምትሠራበትን ይህን እድል የሰጠሽን እግዚአብሔርን አመስግነው፡፡

አንድ ጸሐፊ «በሲዖል የሚኖሩ ኃጥአን ሁሉ ለእግዚአብሔር ንስሐቸውን ለማቅረብ በምድር ላይ የአንድ ሰአት ወይም የአንድ ደቂቃ ሕይወትን መኖር አጥብቀው ይሻሉ» ሲል ጽፏል፡፡

ምንም ያህል አጭር ቢሆንም እንኳን የኃጢአቶቻቸውን ሙሉ ኑዛዜ በማቅረብና «ጌታ ሆይ እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ» /ሉቃ 18፣13/ የሚለውን የቀራጩን ቃል በመናገር ይቅርታውን የሚጠይቁበት የአንድ ደቂቃ ጊዜ ይፈልጋሉ፡፡ እግዚአብሔር ዛሬውኑ ነፍስህን ሊወስዳት ቢወስን ከዚህች የሕይወት ጊዜህ ላይ ጥቂት የንስሐ መግቢያ ደቂቃ





እንድትኖርህ አትመኝምን? ጌታ ሆይ ሐብቴን ለድሆች የማከፋፍልበት ጥቂት ደቂቃ ስጠኝ አትለውምን? ጌታ ሆይ፣ ከተጣላኋቸው ሁሉ ጋር እንድታረቅና ጥፋተኞች እነርሱ ቢሆኑም እንኳን ይቅርታ እንድጠይቃቸው ጥቂት ደቂቃ ስጠኝ አትለውምን? አዎ! ጌታ ሆይ! ዙሪያዬን የከበቡኝ እና ሊናገሩ የማይችሉትን ጨምሮ ሁሉንም ኃጢአቶቼን የምናዘዝበት የተወሰነ ደቂቃ ያስፈልገኛል ትላለህ፡፡ ሙሽራው በመጣ ጊዜ ተዘጋጅተው የነበሩት ከርሱ ጋር ሲገቡ በኋላ የቀሩት ቈነጃጅት መጡና «ጌታ ሆይ ክፈትልን አሉ፡፡ እርሱ ግን መልሶ እውነት እላችኋለሁ አላውቃችሁም አለ፡፡» /ማቴ 25፣10-12/

አዎ! ለሰጠህ ሕይወት እግዚአብሔርን ለምን አታመሰግነውም? እግዚአብሔርን የሚያስደስቱ ብዙ ነገሮች መሥራት ስለምትችልበት፣ ሰዎችን ስለምታስደስትበት እና መንግሥተ ሰማይን ስለምታተርፍበት፣ ንስሐ ገብተህም መንፈሳዊ ሕይወት ስለምትመራበት [illegible] ቀን እግዚአብሔርን ለምን አታመሰግነውም?

www.ethiopianorthodox.org



ከፍተኛ የገንዘብ ሃብት ወይም የስልጣን ደረጃ ካላገኘህ በስተቀር እግዚአብሔርን አታመሰግነውምን? ምናልባት እንደዚህ ያለው ሃብት ወይም ስልጣን መጥፊያህ ሊሆን ቢችልስ በእርሱም ምክንያት የላይኛይቱን መንግሥት ብታጣስ እንዴት ታውቃለህ?

6. ስላደግህበት ሃይማኖታዊ አካባቢ እግዚአብሔርን አመስግነው፤

ስለጥምቀትህ የተጨነቁ፣ የጌታን መንገድ ያስተማሩ እና ይህንን መንገድ ከመከተል ያልከለከሉ ቤተሰቦች ስለሰጠህ እግዚአብሔርን አመስግነው:: አሁን ወደ ደረስህበት የመንፈሳዊ እውቀት ደረጃ እስክትደርስና ድኅነትህን እስክትረዳ ድረስ ስለጠበቁህ ስለቤተክርስቲያን አገልጋዮች እግዚአብሔርን አመስግነው::

እውነተኛ ሕይወትን መማር ትችል ዘንድ መልካም አርአያ የሚሆኑህን በመንገድህ ስላስቀመጠልህ፣ በመንፈሳዊ መንገድ እንዲመሩህም ስለሾመልህ እግዚአብሔርን አመስግነው::

በአሁኑ ሰአት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመሆንህ አመስግነው:: በዚህች ቅጽበት ብዙ ወጣቶች የነፍሶቻቸውን





ድኅነት ረስተው በተለያዩ የዓለም መዝናኛ ስፍራዎች ራሳቸውን ሲያስደስቱ ይገኛሉ:: ነገር ግን አንተ እዚህ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለሆንህ ቤተ ክርስቲያንም ልትነጥላት የማትችላት የሕይወትህ አንድ ክፍል ስለሆነች እግዚአብሔርን አመስግነው::

በዓለም እንዳሉት እንደሌሎቹ ያልሆንከው በአንተ ላይ ካለው ከእግዚአብሔር ጸጋ የተነሳ አይደለምን? ከመካከላችሁ እግዚአብሔር በቤቱ ስላቀፈው ወደ ማደሪያውም ስላስገባው እግዚአብሔርን የሚያመሰግነው ማነው?

ወደ ቤቱ እንዳትመጡና ከልጆቹ ጋር እንዳትሆኑ የሚያደርጓችሁን እንቅፋቶች ስላስወገደላችሁም እግዚአብሔርን አመስግኑት:: የተለያዩ መሰናክሎች ብዙ ሰዎችን ወደ ቤተክርስቲያን እንዳይመጡ ያደናቅፉአቸዋል:: ለምሳሌ ያህል የሥራ ሰአቶቻቸው ከቤተ ክርስቲያን መሄጃ ሰአቶቻቸው ጋር ይጋጫሉ፣ የጤናቸው ሁኔታ፣ ለብዙዎቹ ከቦታ ቦታ የሚያደርጉአቸው የሥራ ጉዞዎች፣ ቤተ ክርስቲያን በሌለባቸው የገጠር አካባቢዎች መኖር ወይም ቤተ ክርስቲያን ወደሌለባቸው ሃገሮች መሰደድ እና ሌሎች ተመሳሳይ እንቅፋቶች ይገጥሙአቸዋል:: አንተ ግን ከነዚህ

www.ethiopianorthodox.org



እንቅፋቶች አንዱ እንኳን ስላላጋጠመህ እግዚአብሔርን አመስግነው።

ከእግዚአብሔር ልጆች ጋር ያለህ ህብረት መንፈሳዊ ጥንካሬን ስለሰጠህ እግዚአብሔርን አመስግነው። የእግዚአብሔር ልጆች በመንፈሳዊ ሕይወትህ እንድታድግ ሁልጊዜ ወደፊት ይገፉሃል። ከእነርሱም ጋር መንፈሳዊ ቁም ነገሮችን የምትለዋወጥበትን የተቀደሰ አካባቢ ታገኛለህ። በተሳሳተ አቅጣጫ ብትሄድና መንፈሳዊ ያልሆነ ጠባይ ብታሳይ እንኳን የነርሱ ጠባይ ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ እንድትመለስ ያደርግሃል። ከነርሱ ጋር ያለህ ግንኙነት ከቤተ ክርስቲያን ጋር ያለህን ህብረት እና በቤተክርስቲያን ውስጥ የምትሠራቸውን ሥራዎች እንዲሁም የምታደርጋቸውን ግንኙነቶች ያጠነክርልሃል። ከዚህ በተጨማሪ መጽሐፍ ቅዱስ «ድካማቸው መልካም ዋጋ አለውና አንድ ብቻ ከመሆን ሁለት መሆን ይሻላል። ቢወድቁ አንዱ ሁለተኛውን ደግሞ ያነሣዋልና።» /መክ 4፣9-10/ እንዳለ ስሜቶችህን የሚያረካ ንጹህ እና መንፈሳዊ ጓደኝነትን ከነርሱ ታገኛለህ። ታዲያ ለዚህ እግዚአብሔርን ማመስገን ተገቢ አይደለምን?





እያንዳንዱ መንፈሳዊ ጓደኛ እግዚአብሔርን ሊያስመሰግን የሚችል ሃብት ነው። ለመንፈሳዊ አባትህ እና መምህርህ እንዲሁም በመንፈሳዊ ሕይወትህ ለረዳህ ለማንኛውም ሰው እግዚአብሔርን ልታመሰግን ይገባል። በመንገድህ ስላስቀመጣቸውና ስለተጠቀምህባቸው ሰዎች እግዚአብሔርን አመስግነው። እነርሱን ላንተ የላከልህ እግዚአብሔር ነውና።

7. እንደ ኃጢአታችን ስላላደረገብን እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን።

ነቢዩ ዳዊት በመዝሙር 103 ውስጥ «ነፍሴ ሆይ፣ እግዚአብሔርን ባርኪ አጥንቶቼንም ሁሉ፣ የተቀደሰ ስሙን። ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን ባርኪ፣ ምስጋናውንም ሁሉ አትርሺ፣» በማለት ይጀምርና «እግዚአብሔር መሐሪና ይቅር ባይ ነው፣ ከቁጣ የራቀ ምሕረቱም የበዛ...እንደ ኃጢአታችን አላደረገብንም፣ እንደበደላችንም አልከፈለንም ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል፣ እንዲሁ እግዚአብሔር ምሕረቱን በሚፈሩት ላይ አጠነከረ። ምሥራቅ ከምዕራብ እንደሚርቅ፣ እንዲሁ ኃጢአታችንን ከእኛ አራቀ። አባት ለልጆቹ እንደሚራራ እንዲሁ እግዚአብሔር ለሚፈሩት ይራራል፤ ፍጥረታችንን

www.ethiopianorthodox.org



እርሱ ያውቃልና፣ አቤቱ አቤቱ እኛ አፈር እንደሆንን አስብ» /መዝ 103፣8-14/ ሲል አጠቃሏል።

እግዚአብሔር ለኛ እጅግ ብዙ ነገር እንዳደረገልን ስናስበው የሚደንቅ ነው። ምሕረቱን አሳየን እንጂ አልቀጣንም! በኃጢአት ዓዘቅት ውስጥ ሆነን በጠራነው ጊዜ እርሱን በመቃወም ኃጢአት እንደሠራን እና ትእዛዞቹን እንደሰበርን ሳይቆጥርብን አብዝቶ በፍቅር መለሰልን በፍቅሩና በርህራሄው የኃጢአትን አስከፊነት እንድንረዳ አደረገን። ለዚህ ሁሉ ሥራው ታዲያ አብዝተን እናመሰግነውምን?

ወደ ኃጢአቶቹ የሚመለከት እና አስከፊነታቸውን የሚረዳ ሰው፣ እግዚአብሔር ምን ያህል መሃሪ እና ኃጠ አተኛን ታጋሽ እንደሆነ ተረድቶ ይደነቃል።

ካንተ ኃጢአቶች የቀለሉ ስንቶቹ ኃጢአቶች ናቸው አስከፊ ቅጣቶችን የተቀበሉት። ሐናንያና ሰጲራ የገንዘባቸውን የተወሰነ ክፍል በማስቀረት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስን በዋሹ ጊዜ ውጤታቸው ለንስሐ እንኳን እድል ሳያገኙ ባሉበት ወድቀው የሕይወታቸው ፍፃሜ ነበር የሆነው። ይሁንና ምን ያህል ሰዎች ናቸው በየቀኑ ደጋግመው የሚዋሹት? ብዙ ሰዎች ካህናትን እና የካህናት አለቆችን በየእለቱ ቢዋሹም





እግዚአብሔር ግን እነርሱን ከመቅጣት ይታገሣል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ደንቆሮ የሚለውም ሁሉ የገሃነመ እሳት ፍርድ ይገባዋል» /ማቴ 5፣22/ እንዳለ ግን አስተውል። እኛ ሁላችን ይህንን ቃል ወይም ከዚህ ጋር ተመሳሳይነት ያለውን ቃል ምን ያህል ጊዜ ተናግረን ንስሐ ገብተናል እግዚአብሔርስ የሲኦል እሳት አደጋ ሳይደርስብን ምን ያህል ጊዜ ይቅር ብሎናል ?

ንጉሱ ሄሮድስ በዙፋን ተቀምጦ ሳለ «ሕዝቡም፣ የእግዚአብሔር ድምጽ ነው የሰውም አይደለም ብለው ጮኹ ሄሮድስ ግን በሰዎች ዘንድ ራሱን ስላከበረና ለእግዚአብሔርም ክብር ስላልሰጠ ያን ጊዜ የጌታ መልአክ መታው በትልም ተበልቶ ሞተ» /ሐዋ 12፣22-23/ እንደተባለ እኛም ይህ እንዳይሆንብን በሰዎች ዘንድ ክብር ስናገኝ ክብሩን ለእግዚአብሔር ሰጥተን ዝም እንበል እግዚአብሔርም አይቀጣንም።

ካህኑ ዘካርያስ በእርጅና ዘመኑ ልጅ ማግኘቱን ስላላመነ ልጁ እስኪወለድ ድረስ አፉን ዲዳ በማድረግ እግዚአብሔር ቀጥቶት እንደነበር እናስታውሳለን።

www.ethiopianorthodox.org



ከእግዚአብሔር ምህረት የተነሣ አለመቀባታችን እንጂ ሁላችንም ከዘካርያስ የበለጠ ኃጢአት በየቀኑ እንሠራለን።

ታዲያ እንደኃጢአታችን ያላደረገብንን እግዚአብሔርን እናመሰግነውምን? እግዚአብሔር በታላቅ ትእግስት ያለፋቸውን በየእለቱ ምናልባትም በየሰአቱ የሠራናቸውን በርካታ ኃጢአቶቻችንን እስኪ እንቁጠራቸው ይህም ሆኖ ግን በሕይወት አለን እግዚአብሔርም በመሐሪነቱ ወደ ንስሐ ይመራናል። የኃጢአቶቻችንን ብዛት ስንረዳ ድንቅ ለሆነው ትእግስቱ እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን። አንዳንድ ሰዎች ደግሞ እንደ እኛ ኃጢአተኞች መሆናቸውን ስለማያምኑ ከኛ ጋር ለምስጋና አይቆሙም። ቅዱስ ጻድቅ እና ቅን ፈራጅ የሆነው እግዚአብሔር ግን እኛ ባናመሰግነውም እንኳን በየእለቱ ደጋግመን የምንሠራቸውን ብዙ ኃጢአቶች ታግሶ ተሸክሞልናል። በአለም ላይ ያሉ ሰዎች በሁሉም ጊዜያት አስቀድመው የሠሩአቸውን፣ አሁን እየሠሩአቸው ያሉትን፣ እና ወደፊት የሚሠሩአቸውን ሁሉንም ኃጢአቶቻቸውን ተሸክሞአል። አስቀድሞ እንዳደረገው እንደፈርዖናውያን በታላቅ ወረርሽኝ እንደ ሰዶማውያንም በጥፋት ውሃ እና በእሳት አላጠፋንም።





ታዲያ በጉልበቶችህ ተንበርክከህ «ጌታ ሆይ ስለታገሥኸኝ እስከ አሁንም ድረስ ኃጢአቶቼን ታግሠህ ስላላጠፋኸኝ አመሰግንሃለሁ። በእውነት ጌታ ሆይ አንተ መልካምና ርህሩህ ነህ» አትለውምን?! «አምላክ ሆይ እንዳንተ ያለ ማን ነው? » / 71፣19/ «አቤቱ ከአማልክት የሚመስልህ የለም እንደሥራህም ያለ የለም።» /መዝ 86፣8/ የሚለው የነቢዩ ዳዊት አባባል እንዴት እውነት ነው!

በአንተም ላይ ሆነ በሌሎች ላይ እግዚአብሔር በሠራቸው ድንቅ ሥራዎች እንዲሁም አድናቆት በምትሰጣቸው በመልካም ባሕርያቱ መመሰጥ መልካም ነው። ርህሩህ፣ መልካም፣ የሚወደድ፣ ይቅር ባይ፣ ታጋሽና «ፍጥረታችንን የሚያውቅ እኛ አፈር እንደሆንንም የሚያስብ...» /መዝ 103፣14/ እንደየሥራችንም የሚያፅናናን ስለሆነ እግዚአብሔርን አመስግነው።

8. ለሚወደደው ትህትህው እና ጥበቃው እግዚአብሔርን አመስግነው።

እግዚአብሔርን ለአንተ፣ ለጓደኞችህ፣ ለወዳጆችህ፣ ለረዳቶችህ እና ለሌሎች ሰዎች ሁሉ ስላለው ተወዳጅ ትህትናው አመስግነው እንዲሁም ለቤተሰቦችህ፣ ለቤተ

www.ethiopianorthodox.org



ክርስቲያን እና ለፍጥረት ሁሉ ላደረገው ትህትናው አመስግነው:: ለሰዎች ሁሉ በሕብረት እና በግል ስላለው ትህትናው አመስግነው::

እስኪ ከራስህ ጋር ለብቻህ ተቀምጠህ ከልደትህ ጀምረህ ያሳለፍከውን ሕይወትህን ቃኘው:: ምን ያህል ልመናዎችን ከእግዚአብሔር ለምነህ ምን ያህሉን መለሰልህ ? ከእንቅፋቶችህ ምን ያህል ጊዜ አዳነህ? ያልተዘጋጀህባቸውን ምን ያህሉን ፈተናዎች እንድታልፍ አደረገህ ? ምን ያህል ችግሮችን ፈታልህ ? ምን ያህል ጊዜ ፈወሰህ ? አንተስ ለሰዎች ያልተገለጹ ምን ያህል ኃጢአቶችን ሠራህ ? ምን ያህል ጊዜያት እግዚአብሔር በአገልግሎቶችህ እና በሥራዎችህ ውስጥ ከአንተ ጋር ነበር ? ምን ያህል ጊዜ በሌሎች ዓይኖች ፊት ሞገስን ሰጠህ? ምን ያህል ማሰናክሎችን አሳለፈህ? ያደረገልህን የፍቅር ርህራሄ መቁጠር ትችላለህ ? ይህን ሁሉ ማወቅ እንደማይቻልህ አምናለሁ:: ለምትወዳቸው ሁሉ ያለው ትህትናው እና ያለጸሎትና ያለጥያቄ ከእርሱ ጸጋ እና ፍቅር የተነሣ ወደ አንተ የሚመጡት መልካም ነገሮች ሁሉ ከተጨመሩ ከቁጥር በላይ የሆኑ እጅግ ብዙዎች ናቸው::





እነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች የእግዚአብሔርን ትህትና ግልፅ አድርገው ፊትህ ላይ ያስቀምጡልሃል:: ስለዚህም በእያንዳንዱ ሥራ ውስጥ በተለይም አንተ ብትረሳቸውም እንኳን ተመዝግበው የተቀመጡ እና ከእግዚአብሔር በቀር ማንም ሊፈታቸው በማይችላቸው እጅግ ውስብስብ በሆኑት ነገሮች ውስጥ እግዚአብሔርን አመስግነው::

9. ስለጤንነትህ እግዚአብሔርን አመስግነው፤

ማየት ስለቻለ እግዚአብሔርን ያመሰገነው ማነው? አንድ ሰው አይኖቹ በበሽታ ቢያዙና ሕክምና ቢጀምር አስቀድሞ ላላመሰገነበት የማየት ችሎታው ሲታመም ግን የማየት ስጦታ እንዲሰጠው አምላኩን በምስጋና ይጠይቃል::

በእግሮቹ መራመድ ስለቻለ እግዚአብሔርን የመሰገነው ማን ነው? ነገር ግን በጉልበቱ ላይ የመሰበር አደጋ ቢያጋጥመውና የሚራመድበት ክራንች የሚጠቀም ቢሆን ጤና ሆኖ በእግር መራመድ ምስጋና የሚያስፈልገው መሆኑን ይገነዘባል:: ጤና በጤነኞች ራስ ላይ ዘውድ ሲሆን ጣእሙን የሚያውቁት ግን በሽተኞች ብቻ ናቸው የሚለው አባባል እውነትነት አለው::

www.ethiopianorthodox.org



ያለንን ነገር ካላጣነው በስተቀር ጥቅሙን መረዳት አንችልም። ከአካላችን ውስጥ አንዱ ካልተጐዳ በስተቀር የሰውነታችን የሥራ እንቅስቃሴዎች በጤናማ መንገድ ስለተከናወኑ ብቻ ብዙዎቻችን እግዚአብሔርን አናመሰግነውም። ስለዚህ አንተ ባለህበት ሁኔታ መሆንን ፈልገው ብዙ ሰዎች ስላልቻሉ ስለመልካም ጤንነትህ እግዚአብሔርን አመስግነው።

10. ስለመልካም ጤንነትህ እግዚአብሔርን እንደምታመሰግነው ስለ ሕመምህም እግዚአብሔርን አመስግነው፤

ሕመም በራሱ መጥፎ አይደለም፤ ድሃው አልዓዛር በቁስል ተወርሶ ይኖር ውሾችም መጥተው ቁስሉን ይልሱ ነበር። ነገር ግን ይህ ሁሉ በራሱ መጥፎ አልነበረም ከእግዚአብሔርም አልለየውም ነበር። ይልቁንም ለመልካም ሆኖለት ነበር። ለዚህም ነው ወደ አብርሃም እቅፍ በወሰዱት ጊዜ «በሕይወት እያለ ክፉ ነገሮችን ተቀብሏል አሁን ግን እርሱ በዚህ ይጽናናል» ሉቃ /16፣25/ የተባለው።

ታላቁ አባት ቅዱስ ባስልዮስ «ለአንተ መልካም ምን እንደሆነ አታውቅም፣ጤንነት ወይም ሕመም ሊሆን ይችላል፣» ብሏል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለመንፈሳዊ





ጥቅሙ የሥጋ መውጊያ ተሰጥቶት ነበር። «ስለዚህም በመገለጥ ታላቅነት እንዳይታበይ የተሰጠው ነገር ከእርሱ እንዲለይ ሦስት ጊዜ ጌታን ለምኖታል።» /2 ቆሮ 12፣8/ እግዚአብሔር ግን ጸሎቱን አልመለሰለትም ይልቁንም «ጸጋዬ ይበቃሃል» አለው። በተፈጥሯችን ካለብን ሰብአዊ ድካም የተነሣ መልካም ጤንነት እንፈልጋለን፤ ነገር ግን ለእኛ ጠቃሚያችን ምን እንደሆነ አናውቅም። ሕመም ብቻችንን ሊያስቀረን ይችላል ነገር ግን ወደ መንግሥተ ሰማይ እንድንገባ ይረዳናል።

«የአባቶች ገነት /The Paradise of Fathers/» በሚል መጽሐፍ ውስጥ የተገፈ አንድ ታሪክ እንዲህ ይላል። «አንድ የታወቀ ባለጠጋ ሰው የታመመችና ለሞት የደረሰች አንዲት ብቸኛ ልጅ ነበረችው። ከቅዱሳን አባቶች መካከልም አንዱን ልጁ ከሞት ትተርፍለት ዘንድ እንዲጸልዩለት ጠየቃቸው ቅዱሱ አባት ግን ለዚህ ጸጋ እንዳልበቁ ቢናገሩም እርሱ አጥብቆ ለመናቸው። ቅዱሱ አባትም ጸልየው ልጁን ከሞት አተረፉለት። ልጅቷ ግን አባቷ ሞቷን የተመኘበትን ሃፍረት ለአባቷ ያስከተለ አሳፋሪ ሕይወትን መምራት ጀመረች።»

www.ethiopianorthodox.org



ብዙ ሰዎች ከሕመማቸው ያገኙአቸውን በረከቶችና ጥቅሞች ሳይመሰክሩ በሕመማቸው ወቅት የደረሱባቸውን ሥቃዮች ብቻ መናገራቸው የሚገርም ነው:: አንዳንዶቹ በሕመማቸው ወቅት ግራ የመጋባትና የጭንቀት ሁኔታ ላይ ይደርሳሉ:: እግዚአብሔርንም ሳይቀር «ይህን ሁሉ ነገር ለምን አደረግህብኝ? » ብለው ይጠይቃሉ:: አንተ ግን እንደርሱ መሆን የለብህም:: ይልቁንም በሕመምህ ጊዜ ከሕመምህ ስለምትቀበላቸው በረከቶች እግዚአብሔርን አመስግነው:: እግዚአብሔርንም እግዚአብሔር ሆይ ለጸሎትና ለንስሐ የምበቃበትን ተጨማሪ ሰአት እንዲሁም ትሑት እና የሰበረ ልብ ስለሰጠኝ ደካማነቴንም እንዳውቅ ስለረዳኝ ስለሕመሜ አመሰግንሃለሁ እግዚአብሔር ሆይ የሰዎችን ፍቅር እንድረዳ ስላደረገኝ ስለሕመሜ አመሰግንሃለሁ:: ይህ ሕመሜ በአልጋ ላይ በነበርሁበት ወቅት ከኃጢአት የተመለስሁበትን ጊዜ ስለሰጠኝ በተለይም ነፍሴን ለመፈለግና ከአንተ ጋር ለመሆን አስፈላጊዬ ስለነበረ አመሰግንሃለሁ» በለው::





11. እግዚአብሔርን ስለጠበቀን፣ ስለመራን፣ ስለረዳን፣ ስለተቀበለን፣ ስለቀረበን ፍቅሩን ስለሰጠን፣ ስለገዛን እና እዚህች ሰአት ድረስም ስላደረሰን እናመሰግነዋለን::

12. እግዚአብሔርን ስለምታየው መልካም ነገር እና ስለማታየው መልካም ነገር አመስግነው::

በዓይንህ ስለምትመለከተው እና በእምነት ስለምትመለከተው መልካም ነገር እግዚአብሔርን አመስግነው:: መልካም ነገርን በስውር እንድናደርግ የጠራንና የምናደርገውን በስውር የሚያይ እግዚአብሔር በግልጥ ይከፍለናል:: /ማቴ 6፤4-6/ እንዲሁም እርሱን በግልጥ እንድናመሰግነው የሚያስገድዱን ብዙ መልካም ነገሮችን በስውር ያደርግልናል:: አሁን የምንደሰትባቸው ብዙዎቹ መልካም ነገሮች እኛ ካልነበርንባቸው ከረዥም ዘመናት በፊት እግዚአብሔር ለእኛ ያዘጋጀልን ነበሩ:: እስከአሁንም ድረስ ውጤታቸው ወደፊት የሚገለጥ ብዙ መልካም ነገሮችን እያዘጋጀልን ነው:: ለዚህም እናመሰግነዋለን:: አሁንና በሁሉም ጊዜያት ልናያቸው የማንችላቸውን መልካም ነገሮች እያደረገልን ነው::

www.ethiopianorthodox.org



እያንዳንዱ የምንሠራው መልካም ነገር በውስጡ የእግዚአብሔር እጅ አለበት፡፡ በራሳችን ምንም አይነት መልካም ነገር ማድረግ የማንችለው «ያለእኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም» /ዮሐ 15፣15/ ስላለ ነው፡፡ ስለዚህ በእኛ ውስጥ እና ከእኛ ጋር የሚሠራ እርሱ ነው፡፡ እዚህ ላይ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነው» /ፊል 2፣13/ ያለውን ልብ በል፡፡

13. በውስጣችን ስለሚሠራው ጸጋ እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን፡፡

ጸጋ ከምስጋና መዝገባችን መጀመሪያ ላይ ከምናስቀምጣቸው መሠረታዊ ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህንን ሲገልጽም «ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ የሆንሁ እኔ ነኝ፣ ለእኔም የተሰጠኝ ጸጋው ከንቱ አልነበረም ከሁላቸውም ይልቅ ግን ደከምሁ፣ ዳሩ ግን ከእኔ ጋር ያለው የእግዚአብሔር ጸጋ ነው እንጂ እኔ አይደለሁም፡፡» /1 ቆሮ 15፣10/ ብሏል፡፡ በውስጣችን ስለሚሠራው ስለዚህ ጸጋ ሁሉም የምስጋና አይነቶች አይገቡለትምን ?





እግዚአብሔርን የበረከት አንድ አካል ሆኖ ስለተሰጠን በሕይወታችን ውስጥ ስላለው የመንፈስ ቅዱስ ሕብረት እናመሰግነዋለን፡፡ ሐዋርያው «የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን ?» /1ቆሮ 3፣16/ እንዳለው የቅዱስ መንፈሱ ቤተ መቅደሶች ስላደረገን እናመሰግነዋለን፡፡ በእኛ ያደረው የእግዚአብሔር መንፈስ «ስለኃጢአት ዓለምን ይወቅሳል» /ዮሐ 16፣8/ «ወደ እውነት ሁሉ ይመራናል» /ዮሐ 16፣13/ «እንደናገለግል ኃይልን ይሰጠናል እኛም በሁሉም ቦታ የእግዚአብሔር ምስክሮች እንሆናለን» /ዮሐ 1፣8/

በውስጣችን ስለሚሠራው መንፈስ ሁልጊዜ እናመሰግንምን? በተወሰነ ጊዜ መልካም ነገር ከሠራን ለሠራነው ነገር እግዚአብሔርን እናመስግን ምክንያቱም በእኛ አማካይነት የሚሠራው እርሱ ነውና፡፡ ለእግዚአብሔር ምስጋና ከመስጠት ይልቅ የሠራነውን ሥራ በራሳችን ኃይል የሠራነው ይመስል መታበይ እና ራሳችንን ማመስገን ትልቅ ስህተት ነው፡፡

www.ethiopianorthodox.org



ይህ ትዕቢት በጽድቅ እንዳናድግ የጸጋን ሥራ በውስጣችን ይደብቅብናል:: /ኢዮ 32፣1/ መንፈስ ቅዱስንም እናሳዝናለን:: «የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ» /2ቆሮ 10፣17/ የሚለውን የቅዱስ ጳውሎስ ቃል እናስታውስ:: ምክንያቱም ፈቃድን፣ ኃይልን እና እውቀትን የሚሰጥ እርሱ ነው ያለእርሱም ምንም ነገር ማድረግ አንችልም:: ቅዱስ ጳውሎስ «ዳሩ ግን ከእኔ ጋር ያለው የእግዚአብሔር ጸጋ ነው እንጂ እኔ አይደለሁም::» /1ቆሮ 15፣10/ ካለ እኛ ደካሞች እና ኃይል የሌለን ምን ማለት እንችላለን ? እኛ ማድረግ የምንችለው እግዚአብሔርን ማመስገን እና ውለታውን በምስጋና መመለስ ብቻ ነው:: በዚህ ጊዜ የጸጋ ሥራ በውስጣችን ይጨምራል የመንፈስ ፍሬዎችም ይበዛሉ::

14. ስለሰጠን ታላቅ ድኅነት እግዚአብሔርን እናመስግነው ፤

በቀንና በሌሊት ምስጋና ልንሰጠው የሚገባ ካለፉት ነገሮች ሁሉ የበለጠ እጅግ ጠቃሚ ነገር አለ:: እርሱም በመስቀሉ ላይ የተደረገልን ታላቅ ድኅነት ሲሆን ያለ እርሱ ግን ሁላችንም እንጠፋ ነበር:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ





ለእኛ ሲል ስለተሰቀለ እና በሥጋ ተወልዶ ደሙን ለእኛ ሲል ስላፈሰሰ ከመካከላችን የሚያመሰግነው ማነው? ያለወልድ ሥጋ መሆን፣ መስቀል እና መሞት ከሞት ፍርድ ማንም ሊድን አይችልም ነበር:: ክርስቶስ ግን ለእኛ ሲል ሞቶ በሞቱ አዳነን::

ከመካከላችን በእያንዳንዱ ቀን በእያንዳንዱ ሌሊት የክርስቶስን መስቀል የሚያስታውስ በእርሱም ምስጋና የሚሰጥ ማነው ? ምክንያቱም በእኛ ፈንታ ዋጋ ከፍሎልናል ያለዚህ ዋጋም መልካም ሥራችን፣ ንስሐችን እና ሌላው ማንኛውም ነገር ሁሉ ምንም ጥቅም ሊኖረው አይችልም:: ነገር ግን ክርስቶስ ሞልተን እኛም «... በጸጋው የጸደቅን» /ሮሜ 3፣24/ ሆንን::

ታዲያ ለተቀበልነው ነፃ ድኅነት እግዚአብሔርን አናመሰግነውምን? ምንም ጥረት ያላደረግንበት ያልደከምንበትና ያለእኛ ጥያቄ እግዚአብሔር ለኛ የመቻቸው እኛም በእርግጠኝነት ብቁዎች ያልነበርንበት «ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል፤

www.ethiopianorthodox.org



ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጢአተኞች ሞቶአልና» /ሮሜ 5፤8፤6/ «እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለዓመጸኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቶአልና» /1 ጴጥ 3፤18/ የተባለበት ይህ ድኅነት እንዴት ያለ ታላቅ ፍቅርና መሥዋእትነት የተገለጸበት ነው? ይህንን የድኅነት ሥራ ሁልጊዜ ከፊታችን ልናስቀምጠውና ለዚህም እግዚአብሔርን ልናመሰግነው ይገባል:: እኛ ባናስታውሳቸውም ቤተ ክርስቲያን በተለያዩ በዓላት ይህንን ታስታውሰናለች::

በየዓመቱ ቤተ ክርስቲያን ሰሙነ ሕማማትን እና ስቅለትን ውጤታማ ከሆኑት ጥልቅ ትዝታዎቹ ጋር ታከብራለች ከዚህ የተነሣ እኛም መስቀሉን ልናስታውሰውና ምስጋና ልናቀርብለት እንጂ ልንረሳው አይገባም:: ነገር ግን ይህ ዓመታዊ በዓል ወቅቱ ሲያልፍ ስለምንረሳው ብቻውን በቂ አይደለም:: ስለዚህም ቤተ ክርስቲያናችን በየሳምንቱ ዓርብ የክርስቶስን መስቀል እንድናስታውስበት የጾም ቀን አድርጋ አጽድቃዋለች:: ነገር ግን ይህ ሳምንታዊ መታሰቢያ ብቻ በቂ ስላልሆነ ቤተ ክርስቲያን ይህንን ታላቅ ድኅነት





ለማሰብ በየእለቱ የስድስት ሰአት ጸሎት ሥርዓትን ሠርታልናለች::

እግዚአብሔር ይህንን ታላቅ ድኅነት ስለፈጸመልን በየእለቱ እናመሰግነዋለን:: ይህ ምስጋና በሁሉም አማኞች የሚፈፀም የአለም አቀፋዊቷ ቤተ ክርስቲያን የምስጋና ስብስብ አንድ አካል ነው::

«...ክርስቶስ ሆይ፣ ፍጥረትህን ከጠላት ባርነት ለማዳን ወደ መስቀል በደስታ ፈቅደህ ዓለምን ለመርዳት በመጣህ ጊዜ ሁላችንንም በደስታ ስለሞላኸን እናመሰግንሃለን፤ ክብር ለአንተ ይሁን፤»

15. እርሱን እንድናውቀው ራሱን ስለሰጠን እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን::

በቅዱስ ጎርጎርዮስ የቅዳሴ ጸሎት ውስጥ «እውቀትህን ሰጠኸኝ ሕግህንም ይረዳኝ ዘንድ ሳከህልኝ» ተብሎ ስለተፃፈው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም ስለመልካም የምስራች፣ ስለ እግዚአብሔር፣ ስለሥራው እና ስለባህርያቱ ስለተነገሩት ነገሮች ሁሉ እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን::

www.ethiopianorthodox.org



በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካሉት ቅዱሳን የአንዱ ትምህርት በሚሰበክልን ጊዜ በእርሱ ትምህርት የልቦናችን ዓይኖች ስለሚበሩ እግዚአብሔርን ለማመስገን ዝማሬ እንዘምራለን:: የእግዚአብሔርን ትእዛዞች፣ ሕጎቹን እና ትንቢቶቹን የቀደሙት አባቶቻችን «...በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው» /2 ጴጥ 1፣21/ ተተውልን አልፈዋል:: ስለዚህ ቅዱሳን አባቶቻችን ነቢያትና ሐዋርያት ተተውልን ሳለፏቸው ሃብቶች የምንሰጠው የምስጋና አይነት የተለየ ሊሆን ያስፈልገዋል::

እግዚአብሔርን በቅዱስ መጽሐፍ አውቀነዋል በልጁም አይተነዋል:: «መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው::» /ዮሐ 1፣18/ በእርሱም አባቱን አወቅነው እርሱ ራሱም ለአባቱ «ጻድቅ አባት ሆይ ዓለም አላወቀህም እኔ ግን አውቅሁህ ... እኔንም የወደድህበት ፍቅር በእነርሱ እንድትሆን እኔም በእነርሱ: ስምህን አስታወቅኋቸው አስታውቃቸውማለሁ::» (ዮሐ 17፥25-26 ) በሎታል::





የርሱን መንገዶች እንድናውቅ ራሱን የሰጠን ጌታ ብፁዕ ነው :: ዳግመኛም ትእዛዞቹን ትምህርቶቹን ነቢያቱን እና ቅዱሳኑን እንድናውቅ የማይገባንን ይህን እውቀት ለእኛ እንዲገባን ስለፈቀደልን እና «ቶሎ ይሆን ዘንድ የሚገባውን ነገር» (ራዕ1-1) እንድናውቅ ስለሰጠን እናመሰግነዋለን::

16. ስለገባልን ቃል ኪዳን እናመሰግነዋለን

በሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም ዘላለማዊ ምቾትን ስላዘጋጀልን እናመሰግነዋለን «የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው ከእነርሱም ጋር ያድራል እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ» (ራዕ 21-3) እንዳለ «...እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደእኔም እወስዳችለሁ» /ዮሐ14፥3/ በማለት ቃል ገብቶልናል:: ከዚህ በተጨማሪም «ዓይን ያላየችውን ጆሮም ያልሰማውን በሰውም ልብ ያልታሰበውን እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀውን» (1ቆሮ 2-9) ሊያወርሰንና ከአባቱ ጋር በዙፋኑ ላይ እንደተቀመጠ ከእርሱ ጋር በዙፋኑ ላይ እንቀመጥ ዘንድ (ራዕ3፥21) ቃል ገብቶልናል በምድር ከገባልን ቃል ኪዳን ጋር ተመሳሳይ የሆኑ በሰማይ የገባልን ቃል ኪዳኖችም እነዚህ ናቸው ::

www.ethiopianorthodox.org



እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእኛ ጋር ሲሆን ቃል ስለገባልን እናመሰግነው (ማቴ 28÷20) ዳግመኛም በቃሉ «ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁ» (ማቴ 28 20) ብሏል። እኛን ሊጠብቀን ቃል ስለገባልን እና «የእናንተስ የራሳችሁ ጠጉር ሁሉ እንኳ ተቆጥሮአል። » (ማቴ 10 30) ስላለን እናመሰግነዋለን። እንዲሁም እያንዳንዳችንን «እኔ በእጀ መዳፍ ቀርጬሻለሁ» /ኢሳ 49÷16/ ስላለን እናመሰግናለን።

## 17. ልጆቹና ወዳጆቹ አድርጎ ስለጠራን እናመሰግነዋለን

ፍቁረ እግዚእ ዮሐንስ «የእግዚአብሔር ልጆቹ ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደሰጠን እዩ» (1 ዮሐ 31) አለ። «በሰማይ የምትኖር አባታችን» (ማቴ 6÷9) በላችሁ ጸልዩ ብሎ አስተማረን። ዳግመኛም «ከእንግዲህ ወዲህ ባሮች አልላችሁም ... ወዳጆች ግን ብያችኋለሁ» (ዮሐ 1515) በማለት የራሱ አድርጎ ስለጠራን «በዚህ ዓለም ያሉትን ወገኖቹን የወደዳቸውን እስከ መጨረሻ ወደዳቸው» /ዮሐ 13 1/ ተባለ።

ከርሱ ጋር ያለንን ግንኙነት በቀርንጫፍ እና በወይን፣ በአካል እና በራስ፣ በሲት ሙሽራ እና በወንድ





ሙሽራ መካከል እንዳለ ግንኙነት ይቆጥረዋል።‹‹እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ... በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ፣ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል።» /ዮሐ 15፣5/ ብሏል፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለእርሱ ሲናገር «እርስዋም /ቤተ ክርስቲያን/ አካሉና ሁሉን በሁሉ የሚሞላ የእርሱ ሙላቱ ናት።» /ኤፌ 1፣23/ «ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስ እንደሆነ ባል የሚስት ራስ ነው» /ኤፌ 5፣21/ ይላል። ከዚህ በላይ ደግሞ «የአካሉ ብልቶች ነን።» /ኤፌ 5፣30/ ካለ በኋላ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ሙሽራ እንደሆነች ሲገልጽ «ይህ ምስጢር ታላቅ ነው» /ኤፌ 5፣32/ ይላል። ዳግመኛም መጥምቁ ዮሐንስ ስለ ክርስቶስ እና ስለቤተ ክርስቲያን ሲናገር «ሙሽራይቱ ያለችው እርሱ ሙሽራ ነው።» /ዮሐ 3፣29/ ብሏል።

እግዚአብሔር ከኛ ጋር ያለውን ግንኙነት የፍርሃት ሳይሆን የፍቅር ስላደረገው እናመሰግነዋለን። በመጀመሪያይቱ ትዕዛዝ «ጌታህን አምላክህን በፍፁም ልብህ፣ በፍፁም ነፍስህ፣ በፍፁም ኃይልህም ውደድ» /ማቴ 22፣27/ ብሏል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ፍቅር እንደዚህ ነው፤ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደወደደን እኛ ደግሞ እርስ በርሳችን ልንዋደድ

www.ethiopianorthodox.org



ይገባናል።» /ዮሐ 4፣10/ ብሏል። ዳግመኛም «እግዚአብሔር ፍቅር ነው፣ በፍቅርም የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል እግዚአብሔርም በእርሱ ይኖራል። ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል እንጂ በፍቅር ፍርሃት የለም» /1 ዮሐ 4፣16/ አለ።





## ምዕራፍ ሦስት

### ከምስጋና ጋር ግንኙነት ያላቸው ምግባራት

**እምነት**

የምስጋና ሕይወት እርሱን ተከትለው ከሚመጡት እና ከእርሱም ጋር ከሚተባበሩ ሌሎች ምግባራት ጋር የተያያዘ ነው። በተለይም ከነዚህ ምግባራት መካከል አንዱ እምነት ነው፤ ይህም የመጀመሪያውን ቦታ የሚይዘውንና ያለእርሱም ወደምስጋና ሕይወት ልንደርስ የማንችልበትን በተወሰኑ የእግዚአብሔር ባሕርያት /ሥራዎች/ ላይ ያለንን እምነት ማለታችን ነው።

እግዚአብሔር መልካም ነገሮችን እንደሚያደርግ እና ከነገሮች ሁሉ በላይ ሰዎችን አፍቃሪ እንደሆነ ማመን ማለት ነው።

እግዚአብሔር ሰብእናህን አንተ ከምትወደው በላይ ይወደዋል? ለራስህ ከምትጠነቀቅለት በላይ እርሱ ላንተ ይጠ ነቀቅልሃል፤ ሁልጊዜም መልካም ያደርግ፥ ሰዎችን አፍቃሪ ከመሆኑ የተነሣ አንተ ሳትጠይቀው መልካም ያደርግልሃል፤ ሁሉንም ነገር የሚመለከት የሁሉም ፈጣሪ ነው፤ «እግዚአብሔር ከክፉ ሁሉ ይጠብቅሃል፣ ነፍስህንም

www.ethiopianorthodox.org



ይጠብቃታል፤ ...እግዚአብሔር መውጣትህንና መግባትህን ይጠብቃል» /መዝ 121፤7-8/

እግዚአብሔር ለሰው የሰጠው ነፃነት ያለምንም ቁጥጥር እያንዳንዱን ሰው ዓለምን ሁሉ እየዞረ የፈለገውን እንዲሠራ የሚያደርግ አይደለም::

እዚህ ላይ ይልቁንስ ዓለምን ሁሉ እየዞረ ከጠላት ስለጠበቀህ እግዚአብሔርን አመስግነው:: በእግዚአብሔር ጥበቃ ፍርሃት ከአንተ ስለወጣ በእግዚአብሔር ጥበቃ ስር መሆንህን እወቅ ምክንያቱም የምትፈራው ጠላት ወደአንተ የሚመጣው ከሦስት ምንጮች ሲሆን እነርሱም ከክፉ ሰዎች ወይም ከሰይጣናት ወይም ከአንተ ከራስህ ነው::

ታላቁ አምላክም በእነዚህ በሁሉም ላይ የማዘዝ ስልጣን አለው ከዚህ የተነሳ አንተ እያወቅህም ይሁን ሳታውቅ እነዚህን ነገሮች ስአንተ ደህንነት ሲል ለዘመናት ተከላክሎልሃል:: እግዚአብሔር ለማንም ፍፁም ነፃነትን አልሰጠም ያለበለዚያማ ዓለም በጠፋች ነበር::

ዳዊትም ሲዘምር «እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ባይሆን ሰዎች በእኛ ላይ በተነሱ ጊዜ ቁጣቸው በላያችን በነደደ ጊዜ በዚያን ጊዜ ሕያዋን ሳለን በዋጡን ነበር፤» /መዝ 124፤2-3/





ያለው ለዚህ ነው:: ስለዚህ ከክፉ ሰዎች ስለጠበቀህ እግዚአብሔርን አመስግነው:: «... ማንም ክፉ ሊያደርግብህ የሚነሣብህ የለም» /ሐዋ 18፤10/ ብሏልና::

ምቼም ቢሆን ምንም አይነት ጉዳት ቢደርስብህ ላንተ ጥቅም እንደሆነና በበጎ እንደሚፈፀም ከእርሱም በረከትን እንደምትቀበል እርግጠኛ ሁን:: እግዚአብሔር ወደ በጎ ለሚለውጠው ክፉ ነገር እንኳን ሳይቀር ላጋጠመህ ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን አመስግነው::

ሰይጣናት እንኳን በሚሠሩት ሁሉ ሙሉ ለሙሉ ነፃ አይደሉም:: እግዚአብሔር እንደፈለጉ እንዲሠሩ አልለቀቃቸውም አለበለዚያማ መላ ምድርን ባጠፏት ነበር:: በኢዮብ ታሪክ ውስጥ የሰይጣን ነፃነት ምን ያህል የተገደበ እንደነበር በግልፅ ተቀምጧል::

ሰይጣን እግዚአብሔር ከፈቀደለት በተጨማሪ ገደቦችንና ወሰኖችን በማስቀመጥ የከለከለውን ሌሎች የተወሰኑ ነገሮችን በኢዮብ ላይ ለማድረግ ጠይቋል:: እግዚአብሔርም ሰይጣንን «እነሆ ለእርሱ ያለው ሁሉ በእጅህ ነው፤ ነገር ግን በእርሱ ላይ እጅህን አትዘርጋ» /ኢዮ 1፤12/ አለው:: በሁለተኛው ጊዜ ደግሞ «ሕይወቱን ተወው እንጂ

www.ethiopianorthodox.org



እነሆ እርሱ በእጅህ ነው» /ኢዮ 2፥6/ በማለት ሰይጣን እጁን በኢዮብ ላይ እንዲዘረጋ ፈቀደለት፡፡ ሙሉ ነፃነትን ሳይሰጥ የሰይጣንን ነፃነት የገደበውን እግዚአብሔርን አመስግን፡፡ ይህ የእግዚአብሔር ሥራ የልብ ሰላም ይሰጥሃል፡፡ በዚህም ምክንያት ሰይጣን እና ተከታዮቹ የሆኑትን ክፉ ሰዎች አትፈራም፡፡ ይህ ሰላምና ፍርሃት አልባነት እግዚአብሔርን የምታመሰግንበት በረከት ሲሆን በድፍረትም «እግዚአብሔር ከኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል? » /ሮሜ 8፥31/ የምትልበት ነው፡፡

ስለዚህ የምትኖረው ዘላለማዊ በሆነ ጥበቃ ውስጥ ሲሆን ይህም ምስጋና የሚያስፈልገው በረከት ነው፡፡ የእምነት ሰው በሰላም፣ በእግዚአብሔር ጥበቃ በመተማመን እና ከፍርሃት በራቀ ሕይወት ውስጥ የሚኖር ሲሆን በዚህ እምነትም ሕይወቱ የማያቋርጥ ምስጋና ወደ ማቅረብ ይለወጣል፡፡

አንድን ሰው እንዲያመሰግን የሚያደርገው ይህ እምነት በረከትም ጭምር ነው፡፡ ምንም አይነት ችግሮች በዙሪያው ቢኖሩም እግዚአብሔርን ስለጥበቃው እያመሰገነ በእቅፉ ውስጥ በሰላም ይኖራል፡፡ ይህ የሚሆነው ደግሞ





ተዕእኖ በሚፈጥሩበት በዙሪያው ባሉት ችግሮች ላይ ትኩረት ስለሚያደርግ ሳይሆን ሁልጊዜ በእግዚአብሔር ሥራ ላይ ስለሚያተኩር እና ከነቢዩ ዳዊት ጋር በሙሉ እምነት «በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም» /መዝ 23፥4/ ስለሚል ነው፡፡

የእኛ አጭር ሰብአዊ ራእይ ከዚህ እምነት በተቃራኒው ስለሚሆን ውጤቱም የምስጋና ሕይወት እንዲኖረን አይፈቅድም፡፡ ነገር ግን ይህ ራእያችን ጭንቀት ፍርሃት እና የመለኮት እርዳታ ከእኛ የመራቁ ስሜት እንዲሰማን ያደርጋል፡፡ ሰብአዊ ራእያችን አጭር እና ውሱን ነው፡፡ ምክንያቱም ወቅታዊ የሆኑትን ችግሮች ብቻ እንጂ የሚመጡትን መፍትሔዎች አያይም፡፡ የወቅቱን ስቃይና ሕመም ያያል እንጂ የወደፊቱን ደስታ አያይም፡፡

ስለዚህ እየተሰቃየህ ባለህበት ችግር ውስጥ ሆነህ በእምነትም ውስጥ የምትኖር ከሆነ ብዙ መፍትሔዎችን ታያለህ ደስተኛና ምስጋና የምትሰጥ ትሆናለህ፡፡

በእምነት እና በማየት መካከል ትልቅ ልዩነት አለ፡፡ ማየት ማለት ነገሮችን በዓይኖችህ መመልከት ማለት ሲሆን በማየት ዓይኖችህ ከሚያዩትና ተጨባጭ ከሆነ



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



መልካም ነገር በስተቀር ምስጋና አታቀርብም:: ነገር ግን በእምነት ስትመለከት በእምነት ላየኸው መልካም ነገር ምስጋና ትሰጣለህ በእግዚአብሔር ሥራም በማመን ያ መልካም ነገር እንዳለ ታምናለህ በእምነት የሚመለከት ሰው ዓይን ማየት ያልቻለውን እና ስሜቶች መረዳት ያልቻሉትን ያያል::

የእግዚአብሔርን ሥራ፣ ወደእኛ የሚመጣውን ጸጋውን እና እርዳታውንም ያያል:: ከዚህ በተጨማሪም የወደፊቱን የእግዚአብሔር ሥራ አሁን ላይ እንዳለ አድርጎ ይመለከታል:: በዚህም በመደሰት ምስጋና ያቀርባል:: የእምነት ሰው እግዚአብሔር ወደ ለዓለም መስክ ሲመራው መውጣቱንና መግባቱንም ሲጠብቀው ያያል:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን::» /ሮሜ 8፣28/ በማለት ስለእምነት ተናግሯል::

ይህንን ጥቅስ አጥናው ሁልጊዜም በፊትህ አስቀምጠው:: ይህንንም ካደረግህ የምስጋና ምንጭ ይሆንሃል:: ከዚህ ውስጥ «እግዚአብሔርን ለሚወዱት» የሚለውን ቃል በጥልቀት አስተውለው:: እግዚአብሔርን የሚወዱት ፍቅሩን





ይቀምሱታል ቃል ኪዳኖቹንም ያምናሉ:: ስለዚህም ነገር ሁሉ የሰዎች አፍቃሪ በሆነው በእግዚአብሔር ቁጥጥር ስር ስለሆነ ነገር ሁሉ ለእነርሱ ለበጎ እንደሚደረግ እርግጠኞች ናቸው:: በአንግሩ ለእግዚአብሔር ካላቸው ፍቅር ጋር በሚስተካከል የዘወትር ምስጋና ይኖራሉ:: «ፍቅር ሁሉን ያምናል::» /1 ቆሮ 13፣7/ እንደተባለ የእምነት ሰው እግዚአብሔር ከድረቅ ዓለት ውሃ እንደሚያወጣ ያምናል /ዘጸ 17፣6/ በእግዚአብሔር የሚያምን ሰው በባህር ላይ በምኞት ይራመድ ዘንድ እግዚአብሔር ባህሩን ወደ የብስ ሊቀይርለት እንደሚችል ከሰማይም ምግብ ይሆነው ዘንድ መናን ማዝነብ እንደሚችል ያምናል:: እግዚአብሔር ከርሱ ጋር በአናብስት ጉድጓድ ውስጥ እና በሚቃጠለው ቁጥቋጦ ውስጥ እንደሆነ በእምነት ማየት ይችላል::

## ትዕግስት

እግዚአብሔር ጣልቃ በመግባት ወደ በጎ የሚለውጣቸውን ችግሮች በእምነት ተመልከት:: ሰው የእግዚአብሔርን ሥራ ለማየት ታጋሽ እና ቻይ መሆን አለበት:: ረዥም ጊዜያትን ቢወስዱም በጊዜያቸው ወደ በጎ የሚለወጡ አስቸጋሪ የሚመስሉ ሥራዎች አሉ:: ሰው ሁሉ

www.ethiopianorthodox.org



ያለምንም እንከን በበጎ ፈቃዱ በመረጠው ትክክለኛ ጊዜ የሚሠራውን እግዚአብሔርን መጠበቅ ያስፈልገዋል::

በጻድቁ ዮሴፍ ላይ የተከሰተውን እንደምሳሌ እንመልከት፣ እንደ ባሪያ ተሸጦ በነበረበት ወቅት ምንም እንኳን ይህንን ተቀብሎ በትህትና እና በውዴታ ቢያገለግልም በጲጥፋራ ሚስት የሐሰት ክስ ምክንያት ወደ እስር ቤት ወርዶ ነበር:: እግዚአብሔር በእስር ቤት እንደረሳው እያሰበም ብዙ ጊዜያትን በዚያው አሳልፏል:: ነገር ግን በትክክለኛው ጊዜ የግብፅ ቀዳሚ ገዥ ይሆን ዘንድ ከእስር ቤት በመፍታት እግዚአብሔር መከራውን ወደ በጎ ቀየረለት:: ስለዚህ እንዲህ ሊሆን የሚችለው በትእግስት እና ክፋትን ወደ በጎ ይለውጥ ዘንድ ይችላል ብሎ እግዚአብሔርን አምኖ በመጠበቅ ነው::

ከዚህ በተጨማሪ የመርዶክዮስን እና የሐማን ታሪክ እንውሰድ፣ መርዶክዮስ መስቀያ ግንዶቹን ካዘጋጀለት ከሐማ ብዙ ስቃዮችን ተቀብሏል: ሐማም ሁሉንም ሰዎች እስኪያጠፋ ድረስ በኢ-ፍትሐዊነቱና በጭካኔው ቆይቷል:: እግዚአብሔር ግን መርዶክዮስንና ሕዝቦቹን ለማዳን





በተገቢው ሰዓት ጣልቃ ገብቷል:: ሐማም ለመርዶክስዮስ ባዘጋጀው ግንድ ላይ ተሰቅሎ ሞቷል:: /አስ 7፣10/

ዲዮቅልጥያኖስ በቤተ ክርስቲያን ላይ ያደረሳቸውን መከራዎች ተመልከት:: የብዙ ሰማእታትን ደም ያፈሰሰ ጨካኝ ንጉስ ነበር:: ነገር ግን እግዚአብሔር ጣልቃ በመግባት ሕዝቦቹን የሕይወቱ መጨረሻ አሳዛኝ ከሆነው ከዲዮቅልጥያኖስ አዳናቸው::

ቆስጠንጢኖስ የሃይማኖት ነፃነትን በመፍቀድ በ313 /ቅ.ክ.ል/ የሚላንን አዋጅ ባወጀ ጊዜ ክርስቲያኖች ከስደትና ከመከራ ጥቅምን አግኝተዋል:: በመንፈሳዊነታቸው ጥልቅ ሕይወትን በእምነታቸው ደግሞ ጽናትን ተለማምደዋል::

ከኛ ጋር ለዘላለም የሚኖር ችግር የለም:: በእርግጠኝነት አንድ ቀን ያቆማል:: ነገር ግን በእምነት ላይ የተመሰረተ ትእግስት ይፈልጋል:: የኢዮብን መከራ ተመልከት፤ በጣም አስቸጋሪ እና መላ ሐብቱን ወንዶች ልጆቹን ሴቶች ልጆቹን፣ ጓደኞቹን እና ሚስቱን እስኪያዳርስ ድረስ የተስፋፋም ነበር:: ይህ ሁሉ የተወሰነ ጊዜ ላይ የቆመ ሲሆን የተፈፀመው ግን በበጎ እና በመልካም ነው::

www.ethiopianorthodox.org



ሐዋርያው ያዕቆብ «እነሆ በትእግስት የጸኑትን ብፁዓን እንላቸዋለን ኢዮብ እንደ ታገሰ ሰምታችኋል:: ጌታም እንደፈጸመለት ሰምታችኋል ጌታ እጅግ የሚምር የሚራራም ነውና::» /ያዕ 5፥11/ «እግዚአብሔርም ከፊተኛው ይልቅ የኋለኛውን ለኢዮብ ባረከ ... እንደኢዮብ ሴቶች ልጆችም ያሉ የተዋቡ ሴቶች በአገሩ ሁሉ አልተገኙም ... ከዚህም በኋላ ኢዮብ መቶ አርባ ዓመት ኖረ ልጆቹንና የልጅ ልጆቹንም እስከ አራት ትውልድ ድረስ አየ::» /ኢዮ 42፥12-16/

ኢዮብ ከመከራዎቹ ምስጋና የሚገባቸው መንፈሳዊ ጥቅሞችን አግኝቷል:: በሕይወቱም ብዙ በጎ ነገሮችን አትርፏል:: ዳግመኛም አስቀድመው በተገለጹት ታሪኮች ውስጥ መርዶክዮስ ወይም ዮሴፍ ያለመከራና ያለስቃይ ሊያገኟቸው የማይችሉአቸው ጥቅሞች ምን ያህል ከፍተኛ እንደሆኑ መመልከት ይቻላል::ነገር ግን በእምነት እና በትእግስት የእግዚአብሔርን አላማዎች እናያለን በጎ የሆነውን ሁሉ እና በረከትንም ሁሉ እንቀበላለን::





ትሕትና

የምስጋና ሕይወትን በጥልቀት ለመኖር በትሕትና ሕይወት እና በተሰበረ ልብ መኖር ያስፈልጋል::

ትሑት ሰው ምንም ነገር ለርሱ የተገባው እንዳልሆነ አድርጎ ስለሚያስብ ለሁሉም ነገር ምስጋና ይሰጣል::ምንም ያህል ትንሽ ብትሆንም ከእግዚአብሔር በተሰጠው በማንኛውም ነገር ለርሱ እንደማይገባ ከልቡ በመረዳት ያመሰግናል ይደሰታልም::

በአንጻሩ ትእቢተኛ ሰው ካለው የበለጠ ብዙ እንደሚገባው ስለሚያስብ ባገኘው ነገር ላይ ያጉረመርማል:: ከፍተኛ ስልጣን ቢያገኝ እንኳን ለታላቅ ስልጣን ብቁ እንደሆነ በማመን ምስጋና ላይሰጥ ይችላል:: በተጨማሪም ሌላ ሰው ክብር ቢሰጠው ይህ ክብር ደረጃውን ያልመጠነ እንደሆነ አድርጎ ያስባል:: ነገር ግን ትሑት ሰው ራሱን ስለሚያውቅ ማንኛውንም የምስጋና ቃል ለማቅረብ የመታበይ ስሜት አይሰማውም::

ትሑት ሰው የሚያስበው ማንኛውም በጎ ነገር ለርሱ እንደማይገባ አድርጎ ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ተጨማሪ ቅጣቶች እና ግሳጼዎችም እንደሚገቡት ያስባል::

www.ethiopianorthodox.org



ስለዚህ ማንኛውም መከራ ቢደርስበት «እንደኃጢአቶቼ ብዛት ከዚህ የበለጠ ብዙ ይገባኛል እንዲያውም ከሚገባኝ ባነሰ መጠን ከእግዚአብሔር የተላከ ቅጣት ነው» በማለት ምስጋና ይሰጣል:: «ከዘላለማዊው ቅጣት ይልቅ እዚህ በምድር ላይ መቀጣት ለኔ ይሻለኛል» ይላል:: ስለዚህ ትሑት ሰው ቅጣቶቹ ከሠራው በታች እንደተከፈሉት ያስባል:: በማንኛውም ጊዜ ምንም ዓይነት ችግር እና መከራ ሲደርስበት «ጌታ ሆይ እጅግ ትሑት ስለሆንህ አመሰግንሃለሁ! ኦ ጌታዬ እንዴት ያለ ፍቅር ነው! የቁጣ ሳይሆን የምሕረት እጅህ በእኔ ላይ ናት» ይላል::

አንዳንድ ሰዎች በችግሮቹ እና በመከራዎቹ ወቅት እግዚአብሔርን የሚያመሰግነውን ሰው «ብርቱ ቅጣት እና ከአቅም በላይ የሆነ ስቃይ የበዛበት በሽታ ቢሰጠው ምን ሊሆን ነው ? እንዴት በስቃዩ ውስጥ እግዚአብሔርን ሊያመሰግን ይችላል?» ሊሉ እና ጥያቄ ሊያነሱ ይችላሉ:: በምድር ላይ ያሉ መከራዎች የተወሰኑና ጊዜያዊ ቢሆኑም ከጉዳታቸውና ከቋሚነታቸው አኳያ ከዘላለማዊው መከራ ይሻላሉ:: ይሁንና ከእነዚህ በሽታዎች ጋር እግዚአብሔር ጽናቱንና ትዕግስቱን ይሰጣል::»





ፍጹም ዓላማ

አንዳንድ ሰዎች በርከት ያሉ ዓለማዊ ወይም ቁሳዊ ዓላማዎች አሏቸው:: ወደነዚህ ዓላማዎች ካልደረሱ እና ካላሳኩ ይናደዳሉ እግዚአብሔርንም ሊያመሰግኑ አይችሉም:: መንፈሳዊ ሰው ግን አንድ ዓላማ ብቻ አለው እርሱም እግዚአብሔር ነው:: ስለዚህ ዓለም ብታልፍ እርሱን አያስጨንቀውም:: ጠፊ በሆኑት ቁሶቿ ደስታን አይቀዳጅም ደስታዎቿን ስላጣም አያዝንም:: ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ግንኙነት ለእግዚአብሔር ምስጋና የሚሰጥበት ታላቅ ደስታ ያገኛል:: የዓለም ሰዎች የሚደሰቱባቸውን በርካታ ነገሮች ንቆ ይተዋቸዋል:: ይሁንና ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ሕይወቱ እርካታ ያለው ሲሆን በምስጋና የተሞላ እና ደስተኛም ነው::

ዓለምን የመናቅ /የብህትውና/ ሕይወት እና ለዓለም ድንነት የሆነው የእግዚአብሔር ፍቅር ወደ ምስጋና ሕይወት ይመራል:: ቅዱሳን አባቶቻችን በዓለም ውስጥ ምንም ነገር ሳይኖራቸው እየኖሩ በደስታ እና በምስጋና ይኖራሉ:: በተመሳሳይ ግንዛቤ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለራሱና በአገልግሎት ረዳቶቹ ስለሆኑት ሲናገር «የተቀጣን ስንሆን አንገደልም፤ ኀዘንተኞች ስንሆን ዘወትር ደስ ይለናል፤ ድሆች

www.ethiopianorthodox.org



ስንሆን ብዙዎችን ባለጠጎች እናደርጋለን አንዳች የሌለን ስንሆን ሁሉ የእኛ ነው::» /2ቆሮ 6፣10/ ይላል:: ዓለም እኛን ምንም ነገር የሌለን እና ድሆች አድርጋ ትመለከተናለች ነገር ግን ከእኛ ጋር ያለው እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ እና ለእኛም ሁለንተናችን ስለሆነ ሁሉም ነገር አለን:: በሰዎች ፊት ኃዘንተኞች ብንመስልም ሁልጊዜ ደስተኞች ነን:: ስለዚህ የምስጋና ሕይወት ትክክለኛ መለኪያዎችን እና መንፈሳዊ መመዘኛዎችን ይፈልጋል:: ያለእነርሱ ማንም ወደ እውነተኛ ምስጋና እና ወደ ሙሉ መንፈሳዊ ደስታ ሊደርስ አይችልም::

አንተም ደስታህን ምስጋና የማያሰጥ ሆኖ ካገኘኸው ይህንን ለማስተካከል ደስታህን ወደምትመዝንባቸው መመዘኛዎችህ ተመለስ:: ያለበለዚያ ስለደስታ ያለህ አመለካከት ትክክል ላይሆን ይችላል::

ሌሎች ምግባራት

ደስታ፣ ሰላም በችግሮች መካከል ያለ ውስጣዊ እና ውጪያዊ ጽናት እንዲሁም ለእግዚአብሔር የተሰጠ ሕይወትን የመሳሰሉ አስቀድመው የተገለጹ ከምስጋና ጋር ግንኙነት ያላቸው ሌሎች ምግባራት አሉ::





## ምዕራፍ አራት

### የማናመሰግነው ለምንድን ነው ?

1. ምስጋና ከማንሰጥባቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱና ዋነኛው ለእኛ በጎው ነገር ምን እንደሆነ አለማወቃችን ነው::

አንድን ነገር መጥፎ እንደሆነ በማሰብ ምስጋና ባንሰጥም እውነተኛ የሆነ በጎ ነገር ሆኖ ይገለጣል ወይም ወደ በጎ የሚመራ መንገድ ሲሆን እኛ ግን ይህንን አናውቅም::

ከዚህ በመነሳት ይህንን እውነታ ለማረጋገጥ ብዙ ምሳሌዎችን ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰኑትን ደግሞ ከታሪክ ለማስቀመጥ እንሞክራለን:: ሁላችንም በፍፁም ጥበቡ ለእኛ በጎ የሚሆነውን የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ እንመን:: ነገር ግን ሰብአዊ ጥበባችን አጭር እና የተወሰነ ነው:: ቀጥሎ የሚመጣውንም አናውቅም::

ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን የጻድቁ ዮሴፍ መታሰር ነው:: አስቀድሞ ዮሴፍ ያለትክክለኛ ፍትህ ወደ እስር ቤት ከመጣሉ እና እንደባሪያ ከመሸጡ በፊት ይህ ሁሉ ለእርሱ ለወንድሞቹ እና ለአባቱ እንዲሁም ለግብጽና በዙሪያዋ ላሉ ሀገሮች ወደ በጎ እንደሚቀየር ያመነ ማነው ? ወንድሞቹ

www.ethiopianorthodox.org



ባይሸጡት ኖሮ በአባቱ ቤት አጠገብ እረኛ ሆኖ ይቀር ነበር:: ይህ ሁሉ በጎ ነገርም አይደረግለትም ነበር:: ከዚህ በተጨማሪ የጲጥፋራ ሚስት ስሙን በማጥፋት ባትከሰው ኖሮ በጲጥፋራ ቤት ባሪያ ሆኖ ይቀር ለፈርኦንም ጌታ አይሆንም ነበር:: በእርግጥ ጻድቁ ዮሴፍ እንደባሪያ በተሸጠ እና ያለአግባብ በተከሰሰ ወደ እስርም በተጣለ ጊዜ ምስጋናን ባይሰጥም በመጨረሻ ግን ሳይጠራጠር ምስጋናን ሰጠ «እግዚአብሔር ብዙ ሰዎችን በሕይወት ለማዳን ሲል ለበጎ እንዳደረገውም አወቀ» /ዘፍ 50፣20/

ሌላው ምሳሌ:- ድንግል ማርያምና ልጇ ወደ ግብጽ ያደረጉት ስደት ነው:: ከሰይፍና ከሄሮድስ የተደረገው ስደት ለምስጋና ብቁ አልነበረምን? በዚህ ስደት የግብጽ ምድር ስለተባረከ እና ኢየሱስ ከድንግል እናቱ ጋር የተጓዘባቸው ቦታዎች ስለተቀደሱ በመጨረሻም በእነርሱ ላይ አብያተ ክርስቲያናት ስለተተከሉባቸው እግዚአብሔርን ልናመሰግን ይገባል::

ከፊታችን ያለው ጊዜ ምን ይዞ እንደሚመጣ አናውቅም:: አንድ ነገር ግን እናውቃለን:: እርሱም ቀጣዩ ጊዜ በእግዚአብሔር እጅ ውስጥ እንደሆነ እናውቃለን::





ሁሉንም ቀጣይ ነገሮችን በበጎ ፈቃዱ ለማስተዳደር እና ለልጆቹ መልካም ነገር ሊያደርግባቸው በእጆቹ ውስጥ ስላስቀመጣቸው እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን:: ስለዚህ በፍቅር ተሞልተው ከእግዚአብሔር እጅ በሚመጡት ሁሉ ለመልካምነታቸው እንተማመናለን:: በእውነት ታላቅ ልብ በነገር ሁሉ ደስ ይለዋል:: ለሁሉም ነገር ምስጋና ይሰጣል:: ምንም ይሁን ምን ለምንም ነገር ፈጽሞ አይጨነቅም:: ሁሉንም ነገር ያስቀመጠበትና የሚያልፍበት የእምነት ጥንካሬ አለው::

በእምነት በሚጋፈጣቸው መሰናክሎች ሁሉ የእግዚአብሔርን እጅ ያያል:: ስለዚህ በእግዚአብሔር ሥራ ድሎችን እና ደስታን ያገኛል ምስጋናንም ይሰጣል::

ቅዱስ አግናጥዮስ እምነትን በአስከፊ ሁኔታ ስለሚፃረሩት እና በቤተ ክርስቲያን ላይ ብዙ ችግሮችን ስላስከተሉት ሲናገር «መጽሐፍ ቅዱስን የበለጠ እንድናጠናው እና በጥልቀት እንድንመረምረው እንዲሁም አስቀድመን የማናውቃቸውን ሐብቶች እንድናገኝ ያደረጉንን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ጥርጣሬ ያነሱትን ሁሉ እናመሰግናቸዋለን:: በተለይም በጥንት ጊዜያት ቤተ ክርስቲያንን የተፈታተኑ

www.ethiopianorthodox.org



እምነት የሌላቸው ፈላስፋዎች ያንኳቸው የነበሩት ፍልስፍናዎችን እንዲሁ እናመሰግናቸዋለን:: በዚህ ዘመን የነበረው ፈተና ለእግዚአብሔር ምስጋና የምንሰጥበትን በረከት አስገኝቶልናል::» ብሏል::

በዚህ ፈተና ምክንያት የመጀመሪያው የእስክንድርያ ት/ቤት ለዓለም ከቀረበት ከሁሉም የመንፈሳዊ እና የጽሑፍ እውቀቶች እንዲሁም እምነትን ከሚያጠነክሩ የነገረ መለኮት ሳይንስ እና የክርስትና ፍልስፍና ጋር ተመስርቷል:: ሁሉንም ነገሮች ለሰው ክብር መገለጫዎች አድርጎ ስለሰራቸው ልባችንን ለእግዚአብሔር ሥራ በምስጋና እንከፍታለን:: ታሪክን በቀየሩ እጆቹ እንደሰታለን እርሱንም እናመሰግነዋለን::

ሌላው ምሳሌ:- የሰማእታት ደም ነው:: ይህስ ምስጋና ልንሰጥበት የሚገባን በጎ ነገር አይደለምን? አዎን ምክንያቱም የሰማእታት ደም ሰማእታት ሰማእትነትን በሚቀበሉበት ወቅት ሰዎች የተፈጠሩትን ተአምራትና ሞትን በታላቅ ደስታ እንዴት እንደተጋፈጡ ስላዩ እና ስለሰሙ የበለጠ እየሰፋ የሚሄድ የእምነት ፍሬ ነው::





የአንጾኪያው አግናጥዮስ የሮም ሰዎች ለተራቡ አናብስት በመወርወር ሊያጠፉት በመሞከራቸው በትሕትና ገስጿቸዋል::

«ወንድሞቼ በመስመሩ መጨረሻ ላይ በደረስኩ ጊዜ ፍቅራችሁ ስለጎዳኝ ፈራሁ እናንተም የሕይወቴን ጉዞ ዳግመኛ እንድሮጥ ፈለጋችሁ» ያለበትን የታወቀ /ታዋቂ/ መልእክት ላከላቸው ይህንንም መልእክት ከላከ በኋላ በሰከንዶች ውስጥ ለተቀራመቱት ለአናብስት ራሱን አሳልፎ ሰጠ:: የቅዱስ አግናጥዮስ ሕይወት የአሁኑ ትውልድ ሊያስታውሰው እና ምስጋናም ሊሰጠው የሚገባው ድንቅ ትምህርት ነው::

ሰማእትነት ከተቀበለ በኋላ ለእስር ቤት ጓደኞቹ ሊያበረታታቸውና ሊያጠነክራቸው ተገልጾላቸዋል:: ስለዚህ የእርሱ ሰማእትነት በረከት ነበር:: ታዲያ ሰማእትነት ተቀበሉ ለሞተ ማልቀስ ይገባልን? አይገባም:: ይልቁንም በሰማእትነቱ አክሊላትን ስለተቀበለ ልንደሰት እና የረዳውንም እግዚአብሔርን ልናመሰግን እንዲሁም «እግዚአብሔር ሆይ እርሱን እንደረዳህ እኛንም እርዳን» በማለት ይህንን ቃል ልንጠይቀው ይገባል::

www.ethiopianorthodox.org



በተመሳሳይ መንገድ ስለአማኞችና ለእምነታቸው ሲሉ በስደት ስለተበታተኑት ሁሉ እንዲሁ ልንናገር እና በሐዋርያት ስራ ውስጥ «የተበታተኑትም ቃሉን እየሰበኩ ዞሩ» /ሐዋ 8፣4/ ተብሎ የተገለጸውን ልናስታውስ ይገባል:: መበታተናቸው ቤተ ክርስቲያን ከተቀበለቻቸው መከራዎች መካከል አንዱ ነው:: ነገር ግን በትክክለኛው ጊዜ የእሳት ነበልባል ሆነው ወደተለያዩ ሃገራት እየተዘዋወሩ በመበታተናቸው ምክንያት እምነት ስለተስፋፋ በረከት ሆኗል:: ይህስ ታዲያ እግዚአብሔርን የምናመሰግንበት አንድ ነገር አይደለምን ?

በራሱ በጎ የሆነ አንድ ነገር ሲኖር በውጤቶቹ በጎ የሆነ ሌላ ነገር ደግሞ ይኖራል:: ስለዚህም በነዚህ ሁለት ምክንያቶች ምስጋና እንሰጣለን:: ሁለቱም ግን ለበጎ የሆኑ ነገሮች ናቸው እግዚአብሔር ስደትን ወደ በጎ መበታተንን ወደ ስብከት እና ወደ እምነት መለወጥ ይችላል:: ብዙ አብያተ ክርስቲያናትም በየቦታው ይመሰረታሉ:: ስለዚህም እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን:: በበጎ ለተሞላው ቅዱስ ፈቃዱም ፍጹም ሕሊናችንን አስገዝተን እናቀርባለን::





2. ምስጋና የማንሰጥበት ሌላው ችግራችን የወደፊቱን አለመመልከታችን ነው::

ሁላችንም መጪው ጊዜ ምን እንደሚሆን አርቀን ሳንመለከት ከእግሮቻችን በታች ያለውን እና የእለት ኑሮአችንን ብቻ በመመልከት ወደፊት ምን እንደሚከሰት እና በዙሪያችን ባለው ነገር ላይ የእግዚአብሔር ዓላማ ምን እንደሆነ ፈጽመን አስተውለን አናውቅም::

እስቲ ቀጥለው የተቀመጡትን ሁለት ምሳሌዎች እንመልከት:: የዕውሩ ሰው መወለድ:- ይህ ክስተት ምስጋና ልንሰጥበት የሚገባ በጎ ነገር አልነበረምን ?

ይህን ድርጊት የጌታ ደቀመዛሙርት እንኳን ቅጣት እንደሆነ አድርገው አስበዋል:: የማግለል ተግባር በመፈጸምም «ይህ ሰው ራሱ ነው ወይስ ቤተሰቦቹ ናቸው? ኃጢአት የሠራው ማን ነው ?» ስላሉ እምነት ከሌለው ዓለም በተላለፉ ስህተት የሆኑ ሃሳቦች ተጠቅተዋል:: ነገር ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምስጋና የሚገባውን እያንዳንዱን የመለኮት እቅድ በእነርሱ ፊት አስቀምጦአል:: ስለዚህ «የእግዚአብሔር ሥራ በእርሱ ተገለጠ እንጂ ይህ ሰው ወይም ቤተሰቦቹ ኃጢአት አልሠሩም» /ዮሐ 9፣3/ አላቸው::

www.ethiopianorthodox.org



አለበለዚያማ እውርነቱ ከልደቱ ጀምሮ ባይኖር ኖሮ በእግዚአብሔር አምኖ እንዲያመልክ እና ስለ ጌታ እንዲከራከር ያስቻለውን እንዲሁም የማይታየውን የሚያይባቸው ሁለት መንፈሳዊ ዓይኖች እንዲኖረው ያደረገውን ውጤት ያመጣለት ይህ ታላቅ ተአምር አይከሰትለትም ነበር:: ከዚህ የተነሳ ይህ ሰው ታሪክ ውስጥ ተካትቷል የእግዚአብሔርም ሥራ በእርሱ ላይ ተገልጿል:: ለብዙዎችም ማመን ምክንያት ሆኗል:: ይህም እግዚአብሔርን ልናመሰግንበት የሚገባ ትልቅ ጉዳይ ነው::

ይሁንና በአብዛኛው የተከሰቱ ውጤቶችን ካየን በኋላ ካልሆነ በስተቀር ምስጋና አንሰጥም:: ነገር ግን አየነውም አላየነውም ማመናችን የተወሰነ በጎ ነገር እንደሚኖር ድፍረት ይሰጠናል:: እንዲሁም «ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው» /ዮሐ 20፣29/ ከመባሉም በላይ «እምነት ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው::» ተብሎ ተገልጿል:: «ዕብ /11፣1/

ሌላው ምሳሌ የማርያምና የማርታ ወንድም የሆነው የአልዓዛር ሞት ነው፣ የአልዓዛር ሕመምና ሞት ምስጋና





የሚገባው ነገር አልነበረምን ? የማርያምና እና ወደ እርሷ የመጡት አይሁዶች ማልቀስ አዲስ ነገር አልነበረም እርሷም ለኢየሱስ «ጌታ ሆይ አንተ እዚህ ብትኖር ኖሮ ወንድሜ አይሞትም ነበር» /ዮሐ 11፣4/ ብላው ነበር::

ሰዎች እግዚአብሔር ከአልዓዛር ሞት በኋላ የሚሠራውን ቢያውቁ ኖሮ የእግዚአብሔርን ክብር ለመግለጽ ለአልዓዛር ሕመምና ሞት ምስጋና ያቀርቡ ነበር:: አልዓዛር በሞት በአራተኛው ቀን መነሳቱ እምነት የበለጠ እንዲስፋፋ አድርጓል:: /ዮሐ 11፣45/ ምስጋና የሚገባው ነገር መሆኑም የሚያጠራጥር አይደለም:: ነገር ግን አልዓዛር በታመመና በሞተ ጊዜ ሰዎች ምስጋና አልሰጡም ነበር:: ምክንያቱም ሰብአዊ ራእያቸው የተወሰነ ስለነበር አልዓዛርን እስከቀበሩበት መቃብር ድረስ ብቻ ተገዝተው በውጭ እያለቀሱ ቆመው ነበር::

እዚህ ርእስ ላይ የነቢዩ ዳዊትን ችግሮች ሳንናገር አናልፍም:: ነቢዩ ዳዊት ከሳኦል ወይም ከአቤሴሎም ወይም ከሌሎች የገጠሙት ችግሮች ሁላችንን ሊጠቅሙ ወደሚችሉ ድንቅ መዝሙራት ይመራሉ ብሎ ማን ሊያስብ ይችላል ? በጭንቀት ጊዜ ዳዊት ችግሮቹን አስር አውታር ባለው በገና

www.ethiopianorthodox.org



እና በእንቢልታ ይዘምር ነበር። ለእኛም ይህንን ታላቅ ሃብት አውርሶን አልፏል። ታዲያ እግዚአብሔርን ለዚህ ሁሉ እናመሰግነውምን? ዳዊት ከዚህ በተጨማሪ «እግዚአብሔርን ሁልጊዜ እባርከዋለሁ ምስጋናውም ዘወትር በአፌ ነው ነፍሴ በእግዚአብሔር ትከብራለች ገሮችም ሰምተው ደስ ይላቸዋል። እግዚአብሔርን ከእኔ ጋር ታላቅ አድርጉት በአንድነትም ስሙን ከፍ ከፍ እናድርግ።» /መዝ 34፣1-3/ ይል ነበር።

ዳግመኛም «ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን ባርኪ አጥንቶቼም ሁሉ የተቀደሰ ስሙን። ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን ባርኪ ምስጋናውንም ሁሉ አትርሺ።» /መዝ 103 1-3/ እያለ በጭንቀቱ ሁሉ እግዚአብሔርን በአዲስ መዝሙር ያከብር ነበር።

ሌሎች ሁለት ትምህርቶችን ከነቢዩ ሙሴ ሕይወት እንማራለን። ሙሴን መግደል በመፍራት በቅርጫት ውስጥ አስቀምጦ በባሕር ዳርቻ ላይ ባለ ሳር ውስጥ መጣልን ማን ሊያምን ይችላል ? /ዘጸ 2፣3/ ይህ ሁሉ ክብርን አምጥቶአል ልጁም /ሙሴ/ በፈርኦን ልጅ የማደጎ ልጅ ሆኖ በቤተመንግሥት ውስጥ አደገ። ታዲያ ይህ የእግዚአብሔርን





ጥበቃ የሚያሳይ እና ምስጋና ልንሰጥበት የሚገባ ትምህርት አይደለምን?

ሙሴ ፈርኦንን በመፍራት ወደ ምድረ በዳ ያደረገው ጉዞ የብዙዎች ጠባቂ ወደመሆን እንደሚመራው በመጨረሻም በቁጥቋጦ መሃል በእሳት ነበልባል አምሳል እግዚአብሔር እንደሚገለጥለት እና ለአገልግሎት እንደሚጠራው ማን ሊያምን ይችላል? እርሱም ከታላላቆቹ ነቢያት እና የሕዝብ መሪዎች አንዱ ሆነ። እነዚህ ጉዳዮች «የነገር ፍፃሜ ከመጀመሪያው ይሻላል» /መክ 7፣8/ የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ያሳስበናል።

ስለዚህ አስቸጋሪ የሆኑ ጅማሬዎች አይረብሹንም ነገር ግን እነዚህን ነገሮች እግዚአብሔር እንዴት እንደሚፈጽማቸው እንመለከታለን። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን የሐማ አስከፊ እቅድ ነው። ሐማ መርዶክዮስን ስላልሰገደለት እና ክብር ስላልሰጠው ታብዮበት እና ጠልቶት ነበር። ይህ የሚረብሽ ጅማሬ ነበር ነገር ግን እንዴት እንደሚፈጸም ለማየት ጥቂት እንጠብቅ። በአስቴር ትእዛዝ ሕዝቡ ሁሉ የጾሙ ሲሆን ይህም ግልቃ በመግባት ወደ እግዚአብሔር የቀረቡበት መንፈሳዊ ጊዜ ነበር። ሐማን

www.ethiopianorthodox.org



በንጉሡ ፊት ሞገስን አግኝቶ ለነበረው ለመርዶክዮስ ባዘጋጀው መስቀያ ግንድ ላይ ሰቀሉት::

ሁኔታው ሙሉ በሙሉ ከመስቀል ወደ ክብር ተለወጠ:: እግዚአብሔር በሚሠራው ሁሉ ብፁዕ ነው:: በተቀደሰው መልካም ፈቃዱ መርጦ መርከብን በመንገዱ የሚመራው እጁ ብፁዕ ነው::

ሌላ ትምህርት ከያዕቆብ ለመሥዋእትነት መዘጋጀት እንማራለን:: የሚወደውን አንድያ ልጁን እንደሚቃጠል መሥዋእት መሠዋት ለአባታችን ለአብርሃም አሳዛኝ ድርጊት መሆኑ አጠራጣሪ አልነበረም /ዘፍ 22፣2/:: ነገር ግን ይህ ሁሉ ለመልካም ነበር:: ምክንያቱም ይህ ድርጊት የአብርሃምን ታዛዥነት ከማሳየቱም በላይ እምነቱን እና ጽድቁን ገልጾለታል:: «አብርሃም በተፈተነበት ጊዜ ይስሐቅን በእምነት አቀረበ፣ የተስፋን ቃል የተቀበለው በይስሐቅ ዘር ይጠራልሃል የተባለለት እርሱም አንድ ልጁን አቀረበ፣ እግዚአብሔር ከሙታን እንኳ ሊያስነሣው እንዲቻለው አስቧልና፣ ከዚያም ደግሞ በምሳሌ አገኘው::» /ዕብ 11፣17-19/፣ በዚህ ፈተና አባታችን አብርሃም «በእውነት በረከትን እባርክሃለሁ፣ ዘርህንም እንደሰማይ





ከዋክብትና በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ አበዛዋለሁ ዘርህንም የጠላቶችን ደጅ ይወርሳል፣ የምድር አሕዛብ ሁሉም በዘርህ ይባረካሉ ቃሌን ሰምተሃልና::» /ዘፍ 22፣17-18/ የተባለበትን የእግዚአብሔር በረከት ተቀብሏል:: በዚህ ፈተና ውስጥ እግዚአብሔርን እንድናመሰግን የሚያደርገንን የመታዘዝ እና የእምነት መልካም ምሳሌን ሰጥቶናል:: ስለዚህ ፈተናው ለአብርሃም ለዘሮቹ እና ለእኛ በረከት ነበር::

ይህ ፈተና ከአብርሃም አንፃርም ሆነ የአብ አንድያ ልጅ ለሆነው /ዮሐ 3÷16/ እና እስከሞት ድረስ ለመስቀል ሞትም እንኳን ታዛዥ ለሆነው /ፊል 2፣8/ ለኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ከሆነው ከይስሐቅ አንፃር በምድር ላይ ለሚገኙት ለሁሉም ትውልዶች ትምህርት እና ምሳሌ ነበር::

ምስጋና ለማቅረብ ምሳሌ ከሚሆኑን መካከል የሐዋርያው የጳውሎስ መታሰር አንዱ ነው::

ጳውሎስ በመታሰሩ ምስጋና የሚሰጥ አለ? አዎን:: በእምነት የተሞላ ሰው በነገር ሁሉ ያመሰግናል:: ጳውሎስ እና ሲላስ ተደብድበውና በእግር ብረት ታስረው ወደ እስር ተጥለው ነበር:: ይሁንና ወደ እግዚአብሔር ይጸልዩ እና

www.ethiopianorthodox.org



መዝሙራትን ይዘምሩ ነበር እስረኞችም ያደምጡአቸው ነበር:: /ሐዋ 16፣23-25/

የእነርሱ መታሰር የፊልጵስዩሱ ወታደር የዳነበትን በረከት አስገኝቷል:: በዚህም ምክንያት ወታደሩ እና ሁሉም ቤተሰቦቹ ተጠምቀዋል:: ከመላ ቤተሰቦቹ ጋር በእግዚአብሔር በማመን ደስታን አግኝቷል:: /ሐዋ 16፣33-34/ ብዙውን ጊዜ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እስር ቤት በነበረበት ወቅት መልእክታቱን የጻፈበት አመቺ ጊዜ አግኝቷል::

3. ምስጋና ማቅረብ ከሚከለክሉን ምክንያቶች መካከል በህብረትም ይሁን በግል ለእያንዳንዳችን እግዚአብሔር ያደረገልንን ጥቅሞች አለማስታወሳችን ነው:: የእኛ ጥፋት መርሳታችን እና አለማስታወሳችን ነው:: ነቢዩ ዳዊት ጥፋቱን በማስታወስ በመዝሙሩ «ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን ባርኪ እጥንቶቼም ሁሉ፣ የተቀደሰስሙን:: ነፍሴ ሆይ፣ እግዚአብሔርን ባርኪ ምስጋናውንም ሁሉ አትርሺ» /መዝ 103፣1-2/ ይላል:: ጥፋቱንም አንድ በአንድ ማስታወሱን ቀጥሏል:: እናንተም ይህንን መዝሙር እንድታነቡና ጥፋቶቻችሁን እንድታስቡ እመክራችኋለሁ





ይህንን ማድረጋችንም እግዚአብሔር ለእኛ ያደረገልንን መልካም ሥራዎች እንድናስታውስ ብርታት ይሆነናል::

እ.ኤ.አ. በ1974 ኮሌራ ሺዎች ሕይወታቸውን ያጠ ብዙ ብት ገዳይ በሽታ ነበር:: ወረርሽኙ ባስከተለው ጉዳት ብዙ ከተሞች በሀዘን ተውጠው ነበር:: ከነዚህ ከተሞች መካከል አንዷን ልዩ ፊቃድ ካገኘሁና ከተከተብኩ በኋላ ለመጎብኘት በቅቼ ነበር:: የተጐሳቆለች እና ሐዘን የወረራት፣ የሚስቅም ሆነ ፈገግ እንኳን የሚል የሌለባት፣ የሬድዮ ወይም የዝማሬ ድምጽ የማይሰማበት ከተማ ሆና ነበር:: ብዙዎች ይጸልዩ እና ለእግዚአብሔር «ካዳንከኝ ይህንን እና ይህንን አደርጋለሁ» በማለት ስእለት ይሳሉ ነበር:: እግዚአብሔር ከዚህ በሽታ ጠ ብቆን እስከዚህች ሰዓት ድረስ ኖረናል፥ እግዚአብሔርን ለዚህ ማዳኑ እና ከሌሎች ገዳይ በሽታዎች እና ወረርሽኞች ላደረገልን ጥበቃ የመሰገነው ማን ነው ?

እግዚአብሔር ለእኛ ያደረገልንን መልካም ነገሮች የረሳን እና የገባናቸውን ቃል ኪዳኖች እና መሐላዎች የዘነጋን ብዙዎች ነን::

እግዚአብሔር ለእኛ ለቤተሰቦቻችን፣ ለጓደኞቻችን እና ለወዳጆቻችን ያደረገልንን ጥቅም ሁልጊዜ ለራሳችን



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



በመንገር እናስታውሰዋለን? ይህንንስ በሕሊናችን እና በማስታዎሻዎቻችን ጠብቀን ለእግዚአብሔር ምስጋና እንሰጣለን? በምድረ በዳ የነበሩት ሰዎች ከእግዚአብሔር የሚያገኙአቸውን ጥቅሞች ለማስታወስ የሰማይ መና ይጠ ባበቁ ነበር:: /ዘጸ 16፣32-34/ ዮርዳኖስን በተሻገሩ ጊዜ የዮርዳኖስ ውሃ ተቋርጦ ለእስራኤል ልጆች ለዘላለም መታሰቢያ ይሆኑ ዘንድ በዮርዳኖስ መካከል ድንጋዮችን አኖሩ /ኢያ 4፣ 4-8/ የእግዚአብሔርን መልካም ምግባራት በምንረሳ ጊዜ ምስጋናችን እና ፍቅራችን ይጠፋል:: ይህም የተለመደ ነው:: ምክንያቱም በአንድ ሰው የተደረገልህን እገዛ ስታስታውስ ያንን ሰው ትወደዋለህ:: ነገር ግን እገዛውን ስትረሳ እርሱን እንድትወደውና እንድታመሰግነው የሚገፋፋህን ምክንያት ታጣለህ::

ምን ያህል ሠራተኞች ሥራ እንዲያገኙ የረዳቸውን እግዚአብሔርን ረስተዋል? ምን ያህል ሚስቶች ባል እንዲያገኙ የረዳቸውን እግዚአብሔርን ረስተዋል? ምን ያህል ሰዎች ችግሮችን በመፍታት እና ከአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ የሚወጡበትን መንገድ በመፈለግ የረዳቸውን እግዚአብሔርን ረስተዋል?





4. አንዳንድ ጊዜ የተቀበልናቸውን መልካም ነገሮች እግዚአብሔር ሳይሆን ከራሳችን ግላዊ ችሎታዎች ወይም ከረዱን ሰዎች ወይም በዙሪያችን ካሉ ሁኔታዎች ያገኘናቸው ስለሚመስለን ምስጋና አንሰጥም::

በዚህ ሁሉ ችሎታዎቻችን ከእግዚአብሔር የተሰጠን ስጦታዎች መሆናቸውን የረዱንንም ሰዎች ደግሞ ለእኛ ሲል እግዚአብሔር በልባቸው ውስጥ እንዳማከራቸው እንዘነጋለን::

5. ከመልካም ሥራዎች ይበልጥ መጥፎ ሥራዎችን ስለምናስብ አናመሰግንም::

ምስጋና የሚገባቸውን በጎ ነገሮች ከህሊናችን ስናስወጣ በረከት ያስገኙ ነጥቦች ይጠፋሉ ችግሮችና መሰናክሎች ግን በውስጣችን ይቆያሉ:: በሕይወታቸው ጥቁር ጠባሳን ጥለው ካለፉ ነጥቦች በስተቀር የሚያስታውሱ ሰዎች አሉ:: ስለዚህም እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች በጎ ነገርን፣ የእግዚአብሔርን ጸጋ እና በረከት ሁልጊዜ በማሰብና በማመስገን በደስታ እና በተስፋ ከሚኖሩት ሰዎች ጋር ሲነፃፀሩ ምስጋና ማጣት ብቻ ሳይሆን ጭንቀት እና ሐዘን ይቆጣጠራቸዋል::

www.ethiopianorthodox.org



6. ምስጋና ማጣት ደስታ የማጣት ምክንያት ሊሆን ይችላል። አስተዋይ ሰው ያለው ነገር ምንም ያህል ትንሽ ቢሆንም ሁልጊዜ ያመሰግናል አስተዋይ ያልሆነ ሰው ግን እግዚአብሔር የፈለገውን ያህል ቢሰጠውም ፈጽሞ አይረካም ምስጋናም አይሰጥም። ሁልጊዜ የበለጠ ስለሚፈልግ ምንም ምስጋና አይሰጥም።

በዚህ ጊዜ አንድ ሰው ጉጉት ወደ ሆዳምነት ሊለወጥ ይችላል ይህም ምስጋናን እንዲያጣ ያደርገዋል።

7. በተጨማሪም አንድ ሰው በሌሎች መንፈሳዊና ስነ ልቦናዊ በሽታዎች የምስጋና ሕይወትን ሊያጣ ይችላል። እነዚህም በሽታዎች ስግብግብነት፣ ራስ ወዳድነት እንዲሁም መረበሽ፣ ተስፋ መቁረጥ ጭንቀት፣ እረፍት ማጣት፣ መጪውን ጊዜ መፍራት በአጠቃላይ ፍርሃት እና ሌሎች ተመሳሳይ በሽታዎች ናቸው።

በነዚህ በሽታዎች የሚሰቃይ ማንኛውም ሰው ሁልጊዜ በነዚህ በሽታዎች የተከበበ እና ግራ የተጋባ ስለሆነ ምስጋና ለማቅረብ አስቸጋሪ ይሆንበታል። ይህንን ሰው ወደ ምስጋና ሕይወት ብትጠራው በመገረም እና ግራ በመጋባት የማቀርበው ለምኑ ነው? ይህ ያለሁበት ሕይወት በቂዬ





አይደለምን? ይላል።እንደዚህ አይነት ሰው ምክር ያስፈልገዋል። ምስጋና ማጣት ነፍስን ይረብሻል የነፍስ መረበሽም ምስጋናን ያጠፋል።

በምስጋና የተሞላ ሰው ለማመስገን ምክንያት አይፈልግም በሰላም የተሞላው ልቡ ለዚህ ምክንያት ይሆነዋል። በምስጋና ያልተሞላ ሰው ግን ሁልጊዜ ይቸገራል ይህም ምስጋና ከመስጠት ይከለክለዋል።

8. ብዙዎች ምስጋናን ከደስታ ጋር ስለሚያያይዙት ምስጋና አይሰጡም።

እነዚህ ሰዎች ደስተኛ የሚያደርጋቸውን መልካም ነገር ይቀበላሉ።ይህ በተፈፀመላቸው ጊዜ ሁሉንም ነገር እዚህ ላይ ይቋጫሉ። የመሰግኑት ዘንድ ይህን መልካም ነገር ማን እንደላከላቸው አያስቡም። ባልተለመደ ሁኔታ በራሳቸው እና በሚያስፈልጓቸው ነገሮች ላይ ብቻ ያተኩራሉ። ምኞታቸውና ደስታቸው እነዚህን ፍላጎቶቻቸውን ማሟላት ብቻ ነው ነገር ግን ይህንን የሚያደርግላቸው ማን እንደሆነ ስለ እርሱ አያስቡም ይህ ታዲያ ራስ ወዳድነት አይደለምን? ነገር ግን አንተ በራስህ ላይ ትኩረት አታድርግ መልካም ነገር ስትቀበልም ምንጩን ተመልከት ለእርሱም ምስጋና

www.ethiopianorthodox.org



ስጥ:: ምስጋና ለማቅረብ እንዳልተመለሱት እንደነበሩት እንደ አስሩ ለምፃሞች አትሁን /ሉቃ 7፣12-18/ ስጭውን ሳታይ ስጦታውን ብቻ አትመልከት::

9. ልናስተውላቸው ከሚገቡን ጠቃሚ ነገሮች መካከል ከውስጣዊ ፍላጐቶቻችን እና ነገሮችን ከምንገመግምባቸው አንፃር ከቆውንና ደጉን ለይተን በሚያስከትለው ውጤት ምስጋናን የምንሰጥበትም ሆነ የማንሰጥበት መስፈርታችን ጠቃሚ ከሆኑት ነገሮች መካከል ዋናው ነው::

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ «አንድ ሰው ጉዳትን በራሱ ላይ ካላመጣ በስተቀር ሰውን የሚጎዳ ማንም የለም» በሚል ርዕስ አንድ ጥሩ አጭር ጽሑፍ ጽፎአል:: በእርግጥ ይህን ሐሳብ ካስተዋልን የምስጋና ሕይወትን እንድናጣ እና በስነ ልቦናዊ ችግሮች ውስጥ እንድንወድቅ ከሚያደርጉን ሌሎች ለእኛ ካላቸው እምነት የማጣት ውጤቶች ማምለጥ እንችልም::

በእውነት አንድ ሰው ወይም ዲያብሎስ እንኳን ሳይቀር አንተን ለመጉዳት ምን ማድረግ ይችላል? አንተ እግዚአብሔርን የምትወድ ቅዱስ እና ጻድቅ ሰው ከሆንህ





ከእግዚአብሔር ጋር በፍቅር ተያይዘህ የመኖር አንድ ዓላማ ብቻ ይኖርሃል:: በዚህ ምክንያትም አንተን የሚጐዳህ ማንም የለም:: ሐዋርያውም «ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ ወይስ ጭንቀት፣ ወይስ ስደት፣ ወይስ ራብ፣ ወይስ ራቁትነት፣ ወይስ ፍርሃት፣ ወይስ ሰይፍ ነው? ስለ አንተ ቀኑን በሙሉ እንገደላለን እንደሚታረዱ በጎች ተቆጠርን ተብሎ እንደተፃፈ ነው:: በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን:: ሞት ቢሆን ህይወትም ቢሆን መላእክትም ቢሆኑ፣ ግዛትም ቢሆን ያለውም ቢሆን የሚመጣውም ቢሆን ኃይላትም ቢሆኑ፣ ከፍታም ቢሆን፣ ዝቅታም ቢሆን፣ ልዩ ፍጥረትም ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ» /ሮሜ 8፣35-39/ ብሏል:: ስለዚህ የእግዚአብሔርን ፍቅር በሕይወትህ ውስጥ ዓላማህ ካደረግህ ከዚህ ዓላማ የሚለይህ የለም በደስታም ትኖራለህ ::

ነገር ግን ከእግዚአብሔር ውጭ የሆኑ ሌሎች ዓላማዎችን እና ፍላጐቶችን እቅድህ ካደረግህ የሚጐዱህ እነዚህ ዓላማዎች ናቸው::

www.ethiopianorthodox.org



ሰዎችን ሳይሆን አንተን የሚጐዳው እነዚህን ፍላጐቶች በውስጥ የሚወደው ልብህ ነው።

አንድ ሰው ከአንተ ገንዘብ ሊወስድ ይችላል አንተም ገንዘብ ካልወደድህ እና መጠኑ ይብዛም ይነስም ትኩረት ካልሰጠኸው ምንም አይነት ጉዳት አይደርስብህም።

አንድ ሰው ወደ እስር ቤት ሊያወርድህ ይችላል አንተ ግን ከእግዚአብሔር ጋር ባለህ ግንኙነት ስለ አእምሮህ፣ ስለሐሳብህ እና ስለነፍስህ ነፃነት ብቻ የምትጨነቅ እንጂ ስለምትኖርበት ወይም ስለምድራዊ ሁኔታህ የማትጨነቅ ከሆነ ምንም አይነት ጉዳት አይሰማህም። ቅዱስ ጳውሎስ ወህኒ ቤት ውስጥ ሆኖ መዝሙር በደስታ ይዘምር ነበር። ሰዎች አንተን ምን ሊያደርጉህ ይችላሉ?

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ለእኔ ሕይወት ክርስቶስ ሞትም ጥቅም ነውና። ነገር ግን በስጋ መኖር ለእኔ የስራ ፍሬ ቢሆን ምን እንደምመርጥ አላስታውቅም በነዚህም በሁለቱ እጨነቃለሁ ልሔድ ከክርስቶስም ጋር ልኖር እናፍቃለሁ ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና» /ፊል 1፣21-23/ ይላል። ሰማዕታት ይሰቃዩ እና ይገደሉ በነበረበት





ሰአት ምንም አይነት የመጐዳት ስሜት አይሰማቸውም ነበር በአንፃሩ ግን አክሊሎችን ይቀበላሉ። ወደ እግዚአብሔር በመሪቻቸው ስቃይ እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ።

ሊያሳዝንህ የሚገባው ብቸኛው ጉዳት ከእግዚአብሔር መለየትህ ነው። በምስጋና ከተሸከምካቸው የክብር ባለቤት የሚያደርጉህ ችግሮች ወይም ጭንቀቶች አይደሉም። ለዚህም ሐዋርያው «ስለክርስቶስ በድካም በመንገላታትም በችግርም በስደትም በጭንቀትም ደስ ይለኛል ስደክም ያን ጊዜ ኃይለኛ ነኝና።» /2 ቆሮ 12፣10/ ብሏል።

10. በምስጋና ሕይወት ውስጥ ትልቁ ችግርህ በራስህ በእግዚአብሔር እቅድ ላይ ከመመስረት ይልቅ አስተሳሰብ ላይ መመስረትህ ነው።

ጉዳዮቻችን ሁሉ በሰብአዊ አስተሳሰባችን ላይ እና በራሳችን መንገዶች መሠረት ሥርአት ማስያዝ እንፈልጋለን። እግዚአብሔር ደግሞ እኛ የማናስተውለው ሌላ እቅድ ይኖረዋል። በዚህ ምክንያት እናዝናለን ምስጋናም አንሰጥም። ለምሳሌ ጥቅማችንና ፍላጐታችን ካልተሟላ እንበሳጫለን። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሁሉም ነገር ይሟላና

www.ethiopianorthodox.org



ብስጭት ባያኘንም ምስጋና አናቀርብም:: ምስጋና በተሞላ ሰው እና ባታጋሽ ሰው መካከል ልዩነት አለ::

ይህ ማለት ጭንቀት ቢኖርም በትዕግስት መሸከም ማለት ሲሆን በአንፃሩ ምስጋናችን ደግሞ በገጠመን ሁኔታ እግዚአብሔርን ልናመሰግንበት የምንችልበትን ድፍረት የሚያሳይ ነው:: እዚህ ላይ ከማየት ወደ ማመን የተሸጋገርንበት ሲሆን ከውጭ በሚወሰነው ሁሉ መልካም የሆነውን ሁሉ በእምነት እናያለን ማለት ነው:: በእርግጠኝነት እግዚአብሔርን ሁልጊዜ በጎ ያደርጋል ምክንያቱም እርሱ ይህንን ማድረግ ይችላል:: በተፈጥሮው ቸር ስለሆነ መልካም እንደሚያደርግልን ማመን አስፈላጊ እና ግዴታ ነው:: ያለንበት ሁኔታ ምንም ያህል አሳዛኝ ቢሆንም የእግዚአብሔር ጸጋ ካልተጨመረበት እጅግ አስከፊ ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን እግዚአብሔር እንደሥራችን ስላልፈረደብን እናመሰግነው ምናልባት ያለንበት መጥፎ ሁኔታ የስህተቶቻችን ውጤት ሊሆን ይችል እንደነበር መዘንጋት የለብንም ለዚህም መውቀስ ያለብን ራሳችንን ነው::





እግዚአብሔርን ግን በሠራናቸው ስህተቶች ስላላዘነብን እና በምክንያቶች ሁሉ ከነዚህ ስህተቶች እንድንወጣ ስላደረገን እናመሰግነዋለን::

ስለዚህ በሰብአዊ አስተሳሰባችን እና ውስን በሆነው ግንዛቤአችን ሳንመሠረት በእግዚአብሔር ጥበብ እና እቅድ ላይ እምነት ሊኖረን ይገባል:: በሚፈጠረው ነገር ሁሉ «ከዚህ ጉዳይ ጀርባ እግዚአብሔር ገለጸውም አልገለጸውም ሁሉንም በጊዜው የሚገልጽ የእግዚአብሔር ጥበብ ስላለ እግዚአብሔርን አመሰግንዋለሁ::» ማለት አለብን::

«ስለአየኸኝ አምነሃል፤ ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው::» /ዮሐ 20፣29/ ይላል:: ይህ በእግዚአብሔር ጥበብ የመታመን እምነት ራስን ወደ ማስገዛት ሕይወት የሚመራ ሲሆን ራስን የማስገዛት /የመስጠት/ ሕይወትም ከምስጋና ሕይወት ጋር ሙሉ ለሙሉ የተስማማ ነው::

በዚህ ሕይወት ውስጥ ለጌታ «ጌታ ሆይ አሁን ካለሁበት የተሻለ ደረጃ ካገኘሽልኝ ወደዚያ ደረጃ ስለምታሸጋግረኝ አመሰግንሃለሁ በእውነት ሁልጊዜ ከሚገባኝ በላይ ትሰጠኛለህ፣ በጥበብህ እና በፍቅርህ ማመኔ ይበቃኛል

www.ethiopianorthodox.org



ሕይወቴንም ላንተ መስጠቴ ምስጋና ያስፈልገዋል» ልንለው ይገባል::

11. አንዳንድ ጊዜ ኃጢአቶቻችንን ስለምንረሳ ምስጋና አንሰጥም::

ኃጢአቶቻችንን ካስታወስናቸው «እንደኃጢአታችን ኣላደረገብንም እንደበደላችንም አልከፈለንም» /መዝ 103፥10/ ስለዚህ እግዚአብሔርን ለማመስገን እንገደዳለን:: ነገር ግን አንድ ቅጣት ብንቀበልም እንኳን ምስጋና ልንሰጥ ይገባናል ምክንያቱም በቀጣዩ ሕይወታችን ዘላለማዊ ቅጣትን ከመቀበል ይልቅ በሕይወት ዘመኑ መጥፎ ነገሮችን እንደተቀበለው እንደ ደሃው አልዓዛር በዚህ ምድር መሰቃየት ይሻለናል:: /ሉቃ 16፥25/

የኃጢአቶቻችንን ክብደት ካስተዋልን እና ወደንስሐ ይመሩን ዘንድ እግዚአብሔር የፈቀዳቸው እንደሆኑ ከተረዳን መከራ በበዛባቸው ስቃዮችም ውስጥ እንኳን ሳይቀር እግዚአብሔርን ልናመሰግን ይገባል::





12. መከራ በመቀበል የሚገኙ በረከቶችን ስለማናስተውል በመከራዎች ውስጥ እግዚአብሔርን አናመሰግንም::

መከራ መቀበል ምስጋና የሚያስፈልገው ስጦታ ነው ሐዋርያው «ስለእርሱ መከራ ልትቀበሉ እንጂ በእርሱ ልታምኑ ብቻ አይደለም» /ፊል 1፥29/ እንዳለ በክብርም የታጀበ ስጦታ ሲሆን «የእግዚአብሔር ወራሾች ነን፣ አብረንም እንድንከበር አብረን መከራ ብንቀበል ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን» /ሮሜ 8፥17/ የተባለውም ለዚህ ነው:: መከራ የክብር መንገድ በመሆኑ ምስጋና ይገባዋል::

ለዚህ ሁሉ ጥቅም እግዚአብሔር መከራን ከወዳጆቹ አላራቀም:: ቅዱስ ጳውሎስ በመስበክ እና በማስተማር ከሌሎች ይልቅ አብልጦ አገልግሏል /1ቆሮ 15፥1/ ይሁንና በ2ቆሮ 11፥23 «እንደ እብድ ሰው እላለሁ፣ እኔ እበልጣለሁ፣ በድካም አብዝቼ በመገረፍ አብዝቼ በመታሰር አትርፌ፣ በመሞት ብዙ ጊዜ ሆንሁ» በማለት እንደገለፀው ከሌሎቹ ሁሉ ይበልጥ ስደት እና መከራ ተቀብሏል::

እግዚአብሔርም ይህን ሁሉ መከራ ከእርሱ አላራቀም:: ነገር ግን ለአገልግሎት እና ለሐዋርያነት

www.ethiopianorthodox.org



ሲመርጠው «ስለ ስሜ ስንት መከራ ሊቀበል እንዲያስፈልገው እኔ አመለክተዋለሁ» /ሐዋ 9:16/ አለ::

ለሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የተናገርነውንም ደግመን እንዲሁ አራት ጊዜ ለታሰረው እና ብዙ መከራዎችና ስድቦች ለደረሱበት የእምነት ዓለት ለሚባለው ለአትናቴዎስ እንዲሁ እንናገራለን:: መላ ዓለም የአንተ ተቃዋሚ ነው ተብሎ ተነግሮለታል:: ነገር ግን እግዚአብሔር ይህ ሁሉ እንዲሆን ፈቀደ:: ምክንያቱም በመከራ ክብር አለ ክብሩም ዘውድ ሲኖረው ዘውዱ ደግሞ የፍቅር መግለጫ ነው:: እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ራሷ ብዙ መከራዎችን የታገሰች ሲሆን በዚህም ከሴቶች ሁሉ የተባረከች ሆናለች::

ለእግዚአብሔር ስትል የተለያዩ መከራዎችን የታገስህ ከሆንህ ይህንን ጥልቅ ትእግስት የሰጠህን እግዚአብሔርን አመስግን ምክንያቱም ለስሙ የተዋረድህ ሆነህ ተቆጥረሃልና /ሐዋ 5፥41/

ወደ መንግስቱ እና ወደ ሕይወት ወደሚመራው ወደ ጠባቡ በር ስለመራህ አመስግነው /ማቴ 7፥14/





13\. በመጨረሻ የምናገረው አንዳንድ ጊዜ በውስጣችን ያለውን መልካም ነገር ምስጋና የማያስፈልገው የተለመደ ነገር አድርገን ስለምንረዳው ምስጋና አንሰጥም::

የተለመዱ ነገሮች አድርገህ ስለምትቆጥራቸው ምስጋና የማትሰጥባቸው እንደጤና እና መጠለያ ያሉ ብዙ መልካም ነገሮች አሉ:: አንተ የተለመዱ ነገሮች አድርገህ ብትቆጥራቸውም ግን እነዚህን ነገሮች የሚፈልጓቸው ሰዎች ጥቅማቸውን ያውቃሉ እነርሱም እነዚህን ነገሮች ካገኙ ለነዚህ ነገሮች እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ::

*«ሳንሰናከልም እንዲጠብቀን፣ በክብሩም ፊት በደስታ ነውር የሌለብን አድርጎ እንዲያቆመን እግዚአብሔርን ሁልጊዜ እናመስግን»*